ኪዳነ ምሕረት

ቁጥር 11

«ከተጻፈው አትለፍ» - ፪



«ሲፈርዱ የሚመጣው ማን ነው?»

የሚለው የ‹‹መምህር›› ዘበነ ለማ ስብከት በቃለ እግዚአብሔር ሲፈተሽ

<u>ኪዳነ ምሕረት</u>፡- የምሕረት ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው፡፡ በኀጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለነበረው ለሰው ልጅ የምሕረት ኪዳን የሆነለት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት (በመስቀል ላይ ሥራው) በመሆኑ ኪዳነ ምሕረት የሚለው ስም የሚገባው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

ቀዳሚ ነገር

በቅዱሱ መጽሐፍ ባለስልጣነት አምነው፣ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ተቀብለው በአነድነት ተጠምደው ከማገለገልይ ይልቅ የየራሳቸው ትናንሽ ጎጆዎች በመቀለስ አንዱን ክርስትና ብዙ ያስመሰሉት ክርስያኖች በልዩነታቸው ዙሪያ በመነጋገር ወደ መስማማት ለመምጣት ጥረት እያደረጉ ባሉበት በዚህ ሰዓት ወደ መለያየት የሚወስድ ስብከት በማቅረብ ይመጣል ተብሎ ተስፋ የሚደረገውን አንድነት የሥጋ ሥራ ተብሎ በተገለጸው በ‹‹መለያየት›› (ገላትያ 6÷21) ለመተካት ጥረት እያደረጉ ያሉ አገልጋዮች በርካቶች ናቸው፡፡

በዚህ መስመር ላይ ያሉት ‹‹መምህር››[1] ዘበነ ለማ የሚታወቁት÷ ሩቅ ለሩቅ ያሉ የሚመስሉትን አብያተ ክርስቲያን በማቀራረብና በልዩነታቸ ዙሪያ እንዲነጋገሩ በማድረግ ሳይሆን ትንሹን ልዩነት ትልቅ በማስመሰል የልዩነቱን ገደል በማስፋት ነው፡፡ ይህን ድርጊታቸውንም በተለያዩ የስብከት ሥራዎቻቸው በግልጽ አሳይተዋል፡፡

በቍጥር 10 የኪዳነ ምሕረት እትም ከ‹‹መምህር›› ዘበነ ስብከቶች አንዱንና ‹‹ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ›› በሚል ርዕስ የተበተነውን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ መሆኑን አሳይተናል፡፡ በዚህ እትም ደግሞ ‹‹መምህር›› ዘበነ ‹‹ሊፈርድ የሚመጣው ማን ነው?›› በማለት ያሰራጩትን የስብከት ሲዲ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር እያስተያየን በተሳሳቱ ትምህርቶች የተሞላ መሆኑን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

ቍጥር 10ን ኪዳነ ምሕረት በተሰራጨበት ወቅት በስልክ ከደረሱን አስተያየቶችና ጥያቄዎች መካከል በ‹‹መምህር›› ዘበነ ስብከት ላይ መልስ መስጠት ለምን አስፈለገ?›› የሚለው ይገኝበታል፡፡ ለዚህ

[1] ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ያስተምራሉ በሚል ተስፋ ‹‹መምህር›› የሚለውን ስም በመስጠት ካሰማራቻቸው ሰዎች መካከል ‹‹መምህር›› ዘበነ አንዱ ናቸው፡፡ እርሳቸው ግን ተስፋ እንደተደረገባቸው ሳይሆኑ ከወንጌሉ ቃል በተለየ መንገድ በመጓዝና ‹‹መምህር››ነታቸው በክርስቶስ ከተገኘው ጸጋ ለሚያርቅ ለተለየ ወንጌል (ገላትያ 1÷6-9) በመቆመ እርሳቸውን መምህር በሚል መጥራት ተገቢ ነው ብለን አናምንምና ከስማቸው በፊት መምህር የሚለውን ባስቀመጥንበት ቦታ ሁሉ ትእምርተ ጥቅስ አድርገናል፡፡

ጥያቄ የሚኖረው መልስ ‹‹መምህሩ›› የተሳሳተ ትምህርት በማስተማር ብዙዎችን እያሳሳቱ በመሆናቸው እርሳቸውም ሆኑ እርሳቸውን ተከትለው እየሄዱ ያሉት ሁሉ ከስሕተታቸው እንዲመለሱ የተሳሳተውን ነገር ለማሳየትና ተመለሱ ለማለት ነው የሚል ይሆናል፡፡

የ‹‹መምህሩ››ን የተሳሳተ ንግግር ቃል በቃል ለማስቀመጥ ጥረት የተደረገ ሲሆን አንባቢው ሐሳቡን በቀላሉ እንዲያገኘው ከሰሩ ጎላ ያለ መስመር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

ቁጥር 11 የኪዳነ ምሕረት እትም በየካቲት 2002 ዓመተ ምሕረት ታትሞ ተሠራጭቶ የነበረ ሲሆን ይህ አሁን እያነበቡት ያሉት እትም በዐዳዲስ ሐሳቦች የተደራጀና በመረጃዎች የዳበረ በመሆኑ ከዚያኛው እትም በተለየ ሁኔታ የቀረበ ጽሑፍ ነው፡፡

እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥
ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን።
አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥
ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን

(ገላትያ 1÷8-9)

ኪዳነ ምሕረት

በ«ማኅበረ እስጢፋኖስ - ኢትዮጵያዊ» የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት የሚታተም መንፈሳዊ መልእክት ነው፡፡

አዘጋጅ፤ ቴዎድሮስ ደመላሽ

+ 251 94 66 57 513

29783 - ዐዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

facebook: www.facebook.com/tewoderodemelash

Email: tewoderosdemelash@gmail.com

‹‹ሊፈርድ የሚመጣው ማን ነው?››

ይህ የ‹‹መምህር›› ዘበነ ስብከት በሲዲ ከመለቀቁ በፊት መጋቢት 12 ቀን 2001 ዓመተ ምሕረት በድምፀ ተዋሕዶ አማካይነት በሬዲዮ የቀረበ ነበር።[2] ‹‹መምህሩ›› በዚህ ስብከታቸው ስለ ክርስቶስ መካከለኝነት ሲያስተምሩ ክርስቶስ አማላጅ ነው የሚለው ትምህርት ዘመን አመጣሽ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ቃል የራቀ፣ እውነትነት የሌለው የስሕተት ትምህርት እንደ ሆነ አስረግጠው ተናግረዋል። ክርስቶስ አማላጅ ሳይሆን ፈራጅ ሊባል እንደሚገባው ትኩረት ለመስጠት የሞከሩት ‹‹መምህር›› ዘበነ፤ ፕሮቴስታንቶች[3] ክርስቶስን አምላክ አይደለም ብለው እንደሚያምኑ አድርገውም አቅርበዋል።

ክርስቶስ አማላጅ ወይስ ፈራጅ?

እንደ ‹‹መምህር›› ዘበነ ለማ እምነት ከሆነ፤

[ፕሮቴስታንቶች] ኢየሱስ ለፍርድ እንደሚመጣ ቢያምኑ እንኳ በአሁኑ ሰዓት ግን ፈራጅ እንደ ሆነ አያምኑም እንደ አማላጅ አድርገው ያስቡታል። ለፍርድ የሚመጣው ግን ማን ነው?

---

[2] "ዘ ኢንድ ታይም" መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 (ገጽ 9)።

[3] መምህሩ በንግግራቸው ‹‹ፕሮቴስታንቶች፣ ፕሮቴስታንቶች›› በማለት የፕሮቴስታንቶችን ሐሳብና ትምህርት ለመቃወም በሚመስል መልኩ ሰብከታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም፤ በዚህ የጽሑፍ መልእክት ማስተላለፍ የተፈለገው የፕሮቴስታንቶች ትምህርት ትክክል ነው የ‹‹መምህር›› ዘበነ ስብከት ስሕተት አለው የሚለውን ሳይሆን ‹‹መምህሩ›› ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የራቀ ሐሳብ እንዴት ባለ መንገድ እንዳቀረቡ በማሳየት ትክክለኛው የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ከእርሳቸው እንግዳ ትምህርት ምን ያህል የራቀ መሆኑን ለመጠቆም ነው።

<u>ኢየሱስ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ እንዴት ለፍርድ የሚመጣ ከሆነ እሱ ከሆነ ዳኛው ፈራጁ እንዴት አማላጅ ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ለመስጠት አይቻልም።</u>

‹‹መምህሩ›› ስለ ክርስቶስ አማላጅነት የሚናገር ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ማግኘት የሚቻል አልመሰላቸውምና ክርስቶስ አማላጅ ነው የሚለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ለማለት እየዳዳቸው ነው። ክርስቶስ አማላጅ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ሲጠቀሱ የሚቀርበው ሐሳብ ‹‹ይህ ጥቅስ መናፍቃን በበረዙት መጽሐፍ ውስጥ እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ውስጥ አይገኝም›› የሚል ነው። ‹‹መምህሩ››ም ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም ዓይነት ሐሳብ እያቀረቡ ያሉት ከዚህ በመነሣት መሆኑ ግልጽ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ምልጃ ምን ይላል?

1. **ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ከክርስቶስ መወለድ ከ701 ዓመት በፊት እንደ ጻፈው በሚታመነው የትንቢት መጽሐፉ ውስጥ፣ ክርስቶስ ምን ዓይነት መከራ እንደሚቀበል በስፋት በጻፈበት ክፍል፤ ‹‹ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኀጢአት ተሸከመ፥ ስለ አመጸኞች ማለደ›› በማለት በበደላችን ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የማንችለውን ኀጢአተኛ የሆንን እኛን ጻድቅ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ (ለማማለድ)**

በመካከል እንደሚገባ ትንቢት ተናግሮ ደግሞም ጽፎት ነበር (ኢሳይያስ 53÷12)። ይህ ትንቢታዊ መልእክትም በስቅለቱ ጊዜ ‹‹አባት ሆይ÷ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› በማለቱ መፈጸሙን ማስተዋል እንችላለን (ሉቃስ 23÷34)።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ÷ ‹‹ስለ አመጸኞች ማለደ›› ማለቱ ክርስቶስን ከክብር ማሳነሡ አልነበረም። እንዲህ የሚሰማቸው ሰዎች በአንዱ ጥቅስ ላይ ልዩ ልዩ አመለካከት ያላቸው መሆኑ ‹‹ኢየሱስ፤ እውነተኛ አማላጅ፣ ጻድቅ ፈራጅ›› በተሰኘው መጽሐፍ ከዚህ በታች በሰፈረው መልኩ ተጽፏል፤

> ‹‹ቅድመ ልደቱ እንዲህ ባለ ሁኔታ ለምልጃ ሥራ እንደሚመጣ የተነገረ ቢሆንም እንዲህ ያለው እውነት አልዋጥ ያላቸው ሰዎች ይህን ጥቅስ ‹ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከኀያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና÷ ከዐመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኀጢአት ተሸከመ፤ <u>ስለ ኀጢአታቸውም ተሰጠ</u>› በሚል ቀይረውታል።[4] በጥቅሱ መለወጥ የሚስማሙና ሐሳቡን የሚጋሩ አንዳንድ ግለሰቦችም ‹በኢሳይያስ 53÷12 ላይ... ማለደ የሚለው ሠርጎ ገብ ቃል ነው

[4] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ (2000) - አጽንዖት የግል።

እንጂ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሊነገር የማይገባ ቃል ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ስለ ዐመፀኞች ሊማልድ ሳይሆን ተላልፎ እንዲሰጥ በመስቀል እንዲሰቀልና የሰውን ልጅ እንዲያድን ነው› የሚል ምክንያት ሊያቀርቡ ሞክረዋል።[5]

ከዚህ የተለየ ሐሳብ ያላቸው አቶ ሚራክ ገብረ ክርስቶስ ደግሞ < ‹ስለ ዐመፀኞች ማለደ› የሚለውን ሐረግ ይዘን ‹ማለደ› ከተባለ አማላጅ የማይባልበት ምክንያቱ ምንድን ነው? ቢባል ምልጃ ከቤዛነት ሥራው አንዱ ንኡስ ክፍል ነው። ጠቅላላ የማዳን ሥራውን አያጠቃልልም ነው መልሱ። ቤዛነቱን በመስቀል እስኪፈጽም ድረስ ለሰው ሁሉ አብነት (‹መምህር›) ሆኖ የትሩፋት ጎዳና ቀይሷልና> ይላሉ።[6]

እነዚህ ሰዎች እንዲህ የሚያደርጉት ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን ልማዳዊ ትምህርት ተቀርቋሪ በመሆናቸው ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪነታቸው ግን ቅድሚያ ሊሰጡ

[5] ወልደ ሚካኤል ቶሎሳ፣ በእንተ ሰማንያ አሐዱ (2005) ገጽ 163።
[6] የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምእመናን የቅዱስ እስጢፋኖስ ጉባኤ፣ ፍኖተ ብርሃን (ጥቅምት 1990) ገጽ 14።

የሚገባው የእግዚአብሔር ቃል ለሚለው እውነት ነበር። ለቃሉ እውነት ቅድሚያ ቢሰጡ ኖሮ የሰው ልጆች መዳን የተከወነው በክርስቶስ የመካከለኝነት (የምልጃ) ሥራ መሆኑን ባስተዋሉ ነበር። <ምልጃ ከቤዛነት ሥራው አንዱ ንኡስ ክፍል> ሳይሆን የቤዛነት ሥራው ምሰሶና ማገር ነው። የምልጃው ሥራ የተሠራው በስብከቱ አልያም በሠራቸው የተአምራት ሥራዎቹ ሳይሆን በመስቀል ላይ ስለ ሰው ልጆች ሲል በከፈለው ዋጋ ነው። ይህን ዋናውንና ብቸኛውን የቤዛነት (የምልጃ) ሥራ <ከቤዛነት ሥራው አንዱ ንኡስ ክፍል> እንደ ሆነ ሊናገሩ የሚዳዳቸው ሰዎች ዋናው (ዐብዩ) የቤዛነት ሥራውን የትኛው ነው ሊሉ ይሆን?

‹በአንድምታ ትርጓሜው ላይ <ኀጢአታቸውን ወደ መስቀል ያወጣል ማለት ኀጢአታቸውን በመስቀል ያስተሰርይላቸዋል፤ ስለ ኀጢአታቸው ለሕማም ለሞት ተሰጠ> በማለት የተቀመጠው ሐሳብ ምንም እንኳ አንዳንዶች ቢቃወሙትም የመስቀል ላይ ሥራው ኀጢአታችንን ሊያስተሰርይ ወይም ይቅርታን ሊያሰጠን መሆኑን በሚገባ ያስረዳል፤ አንድምታው <ያስተሰርይላቸዋል>

በማለት ክርስቶስን በመካከል ማስቀመጡን አንባቢው ልብ ይበል› ››።[7]

2. ‹‹አማለድሁ›› ብሎ የተናገረው ክርስቶስም ሆነ የክርስቶስን ንግግር የጻፈው ወንጌላዊው ሉቃስ ሳይሸማቀቁ ‹‹ጌታም፡- ስምዖን ስምዖን ሆይ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ›› የሚለውን አስተላልፈዋል (ሉቃስ 22÷31-32)። ክርስቶስ ራሱ ‹‹አማለድሁ›› ሲል በግልጽ እየተናገረ እንዲህ ያለ ነገር መጻፍም ሆነ መናገር ክርስቶስን ከአብ ማሳነስ እንደ ሆነ የሚሰማቸው ሰዎች አሉ።

3. ስለ ክርስቶስ መካከለኝነት ሲነሣ ብዙዎችን እያነጋገረ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሮሜ 8÷34 ነው። ክርስቶስ አማላጅ ለመሆኑ እንደ ማስረጃ ሆኖ በሰፊው በማገልገል ላይ ያለው ምንባብ ይህ በመሆኑ ‹‹ይህ ጥቅስ መናፍቃን ለራሳቸው ትምህርት እንዲመች አድርገው ያጣመሙት ጥቅስ ነው›› የሚል ነገር በተደጋጋሚ ይሰማል። በእነርሱ እምነት ይህ ምንባብ የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ፈራጅነት ነው። ጥቅሱ የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ፈራጅነት ሆኖ ከጊዜ በኋላ የተቀየረ አለመሆኑን የቤተ ክርስቲያቱን መጻሕፍት መሠረት በማድረግ ማየቱ ጠቃሚ ነው።

በ1994 ዓመተ ምሕረት በግእዝና በአማርኛ ተዘጋጅቶ በትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት አሳታሚነት ለንባብ የበቃው

[7] ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ ኢየሱስ፤ እውነተኛ አማላጅ፣ ጻድቅ ፈራጅ (ሚያዝያ 2009) ገጽ 22-23።

ዐዲስ ኪዳን፤ በአማርኛ ምንባቡ ላይ ‹‹የሚፈርደው ማነው፤ ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ፤ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ፤ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፤ ስለ እኛም ይፈርዳል›› በማለት ክፍሉ ክርስቶስ አማላጅ እንደ ሆነ ሳይሆን ፈራጅ እንደ ሆነ የሚናገር በማስመሰል ያሰፈሩት ቢሆንም፤ የግእዙ ምንባብ ላይ ግን÷ ‹‹መኑ ዘይኴንን ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ ወተንሥአ እምዉታን፤ ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር፤ ወይትዋቀሥ[8] በእንተአነ››[9] በማለት ከፍርድ ጋር ሳይሆን ከምልጃ ጋር አስታሳስረው ነው ያስቀመጡት፡፡[10]

---

[8] ‹‹ወይትዋቀሥ የሚለውን ቃል አለቃ ኪዳነ ወልድ ‹መውቀሥ፣ መክሰስ፣ መንቀፍ፣ መዘለፍ፣ መምከር፣ ተዋቀሠ፣ ተሟገተ፣ ተከረከረ› ማለት ነው ብለውታል (ኪዳነ ወልድ መዝገበ ቃላት ገጽ 401)፡፡ ስለዚህ ‹ወይትዋቀሥ› የሚለው የግእዝ ቃል ትርጉም ‹ኢንቱግካኔይ› ከሚለው ከግሪክኛው ቃል ጋር አቻ ነው፡፡ ‹ወይትዋቀሥ› ማለት ‹ይፈርዳል› ማለት አይደለም›› (ጌታቸው ተረፈ (መምህር)፣ መልሕቅ (ክፍል ሁለት) (መስከረም 2010 - 2ኛ እትም) ገጽ 179)፡፡

[9] በግእዝና በአማርኛ የታተመው ዐዲስ ኪዳን በዚህ መልክ እንዲዘጋጅ ከፍተኛውን ግፊት ያደረጉትና በጊዜው የለቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የነበሩት አለቃ አያሌው ታምሩ መሆናቸው ይነገራል፡፡ በርግጥ እርሳቸው እንዲህ አድርገው ከነበረ በኋላ ላይ የአቋም ለውጥ አድርገው ነበር ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ‹‹ምልጃ፣ እርቅና ሰላም›› በሚል ርእስ በ1992 ዓመተ ምሕረት ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ ይህን ጥቅስ በግእዙ ‹‹ለእመለሊሁ ያጸድቅ መኑ ዘይኴንን ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ ወተንሥአ እምዉታን ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር <u>ወይትዋቀሥ በእንቲአነ</u>›› በሚል ያስቀመጡት ሲሆን በአማርኛው ደግሞ ‹‹እሱ ቢያጸድቅ የሚኰንን ማን ነው? ሞቶ የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በአብ ቀኝ ተቀምጧል <u>ስለ እኛ ይከራከራል</u>›› በሚል ነው ያሰፈሩት፡፡ ስለዚህ በእርሳቸው እምነት መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ የሚከራከርልን ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ሐሳባቸው ደግሞ ከ1ኛ

ሰዎቹ ‹‹ይፈርዳል›› እንዲልላቸው የሚጠብቁት ቃል ‹‹ወይትዋቀሥ›› የሚለው ነው፡፡ ‹‹ተዋቀሠ›› የሚለው ትርጉም ‹‹ተሟገተ፣ ተከራከረ››[11] ቢሆንም ሰዎቹ ግን ከመሠረተ ሐሳቡ ውጭ በሆነ ሁኔታ ለመተርጐም የተነሣሡበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በልማድ ለገባ ትምህርት ቅድሚያ በመስጠታቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ምንም እንኳ ግእዙ እንደዚያ ባይልም ‹‹ ‹ስለ እኛ ይፈርዳል› ተብሎ የተተረጐመው ስሕተት የሆነው አለ ንባቡ በመተርጎሙ ብቻ አይደለም፤ በሕገ ሰዋስው መሠረት ሲታይ ሐረጉ በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ እንዲገልጽ የተፈለገውን ሐሳብ ስለማይገልጽና ሌላ ትርጉም ስለሚሰጥም ጭምር ነው እንጂ፡፡ በዐማርኛ ሰዋስው ‹ስለ እኛ ይፈርዳል› የሚል ንባብ ‹ለእኛ ይፈርዳል› የሚል ትርጉም ሊሰጥ አይችልም፡፡ የሚሰጠው ፍቺ በእኛ ምትክ፣ እኛን ወክሎ ይፈርዳል የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቃሉን የለወጡት ሰዎች ቃሉ እንዲናገርላቸው የፈለጉትን ‹ለእኛ ይፈርዳል› የሚለውን ሐሳብ አይጠራላቸውም፡፡ እንዲያውም ያልጠበቁትን ትርጉም ይሰጥባቸዋል፡፡ የተፈለገውን ትርጉም ይሰጥ ዘንድ ‹ስለ› የሚለው መስተዋድድ ይፈርዳል ከሚለው ግስ ጋር ሳይሆን

ዮሐንስ 2÷1-2 ጋር ተስማሚ ነው (አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ ምልጃ፣ እርቅና ሰላም (ዐዲስ አበባ፣ 1992) ገጽ 27)፡፡

[10] ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ ዐዲስ ኪዳን በግእዝና በዐማርኛ (ዐዲስ አበባ፣ 1994) ገጽ 644 - አጽንዖት የግል፡፡

[11] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ፣ (1948) ገጽ 401፡፡

ይማልዳል ወይም ይከራከራል ከሚለው ግሥ ጋር ነው ሊሄድ የሚችለው››።[12]

የግሪኩ ትርጉም በዚህ ክፍል ላይ ክርስቶስ አማላጅ እንደ ሆነ ነው የሚገለጸው፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ በሊቃውንቶቿ አስተርጉማ በ2000 ዓመተ ምሕረት ባሳተመችው ሰማንያ አሐዱ ላይ ቃሉን በመቀየር ‹‹የሚፈርደው›› በሚለው ቢያስቀምጡትም የግሪኩ ትርጉም አማላጅ እንደ ሆነ የሚገልጸውን መሸፋፈን የሚችሉበት እድል ስላልነበራቸው ‹‹ግሪኩ <የሚማልደው> ይላል›› በማለት በግርጌ ማስታወሻቸው ላይ አስቀምጠዋል።

ዐዲስ ኪዳን የተጻፈበት የመጀመሪያ ቋንቋ (እናት ቋንቋ) ግእዝ ወይም አማርኛ ሳይሆን ግሪኩ እንደ መሆኑ ከሌሎች ቋንቋዎች ሁሉ ይልቅ ተሰሚነት ሊኖረው የሚችለው እርሱ ብቻ ነበር። ስለዚህ ከአማርኛው ትርጉም ይልቅ ለግሪኩ ትርጉም ትልቅ ግምት በመስጠት በታማኝነት ሊተረጉሙት ሲገባ የግሪኩ መልእክት ለአስተምህሯቸው ሳይመች ሲቀር የራሳቸውን ፈቃድ ማስገባት እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝነው ግልጽ ነው።

4. ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ መካከለኝነት በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ሁለት ያስተላለፈው መልእክት፡- ‹‹አንድ እግዚአብሔር አለና÷ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ አለ÷ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ራሱን ለሁሉ ቤዛ ሰጠ÷ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበር እኔም ለዚህ ነገር

[12] ማኅበረ በኵር፣ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 39 (ሐምሌ 2002) ገጽ 8 - አጽንዖት የግል።

አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤ እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም›› (1ኛ ጢሞቴዎስ 2÷5) የሚል ነው፡፡ ይህን ምንባብ ሰማንያ አሐዱ ምን እንደሚለው እንመለከት፡-

> እግዚአብሔር አንድ ነው፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው[13] መካከለኛውም አንድ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ በግዜውም ምስክር ሆነ፡፡[14]

‹‹መምህር›› ዘበነ በዚህ ጥቅስ ዙሪያ ከአድማጭ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ክርስቶስ ‹‹መካከለኛ የተባለበት ምክንያት ሥጋን ስለ ተዋሐደ ነው ሥጋን በተዋሐደ ሰዓት አስታረቀን...››[15] በማለት አማላጅነቱን አንድ ወቅት ላይ እንደ ነበረ ነገር ግን አሁን ያ የማስታረቅ ሥራ እንደማያገለግል፣ እንደ ቀረ በማስመሰል መልስ ለመስጠት

---

[13] ቤተ ክርስቲያን በ2000 ዓመተ ምሕረት ያሳተመችው ሰማንያ አሐዱ በራሷ ሰዎች አስተርጉማ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት እንዲመች አድርጋ ያሳተመችው መጽሐፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የክርስቶስን መካከለኝነት (የምልጃ ሥራ) በተመለከተ የቤተ ክርስቲያችን ትምህርት አይደለም ለማለት በዚህ መጽሐፍ ላይ የተሠራ ሥራ መኖሩን ሮሜ 8÷34 ላይ የተሠራውን ሥራ በመመልከት ብቻ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም ምንባብ ላይ ግን የክርስቶስ መካከለኝነትን በተመለከተ በአግባቡ የሰፈረ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረ ሲሆን አሁን ግን በክብር ነው ያለው፡፡ በዚህ መልእክት ላይ ግን ‹‹የነበረው›› በሚል በኃላፊ ጊዜ ሳይሆን ‹‹ያለው›› በማለት አሁንም በመካከል መሆኑን እንደ ተጻፈ ልብ ይበሉ፡፡

[14] በ2000 ዓመተ ምሕረት የታተመው ሰማንያ አሐዱ፡፡

[15] ዘበነ ለማ (መምህር)፣ አርቶዶክሳዊ መልስ የተሰኘ የቴፕ ካሴት፡፡

ሞክረዋል፡፡ በዚህ ንግግራቸውም አሁን ሥጋን ያልተዋሐደ እንደ ሆነ በማስመሰል ተናግረዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ፤ ‹‹ኢየሱስ ተነሣ ስንል አሁንም በሥጋው በተዋሐደው ሥጋ ተነሣ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ ለ500 ባልንጀሮች ተገለጠ ታየ… ይህ በሦስተኛው ቀን የተነሣው ክርስቶስ ኃያሉ አምላክ በአርባኛው ቀን አረገ ሲያርግም ደቀ መዛሙርቱ አዩት÷ ሊያዩት የቻሉት በተዋሐደው ሥጋ ስላረገ ነው፡፡…›› የሚል ሐሳብ አስታላልፈዋል፡፡ ለብሶት የነበረውን ያን ሥጋ አክብሮ ይዞት ከሄደና፤ ያ ሥጋ አሁንም በሰማይ ከሆነ ያለው በዚያው በሥጋው እንዳያስታርቀን ምን ይከለክለው ይሆን?

5. ሌላው÷ ጳውሎስ ክርስቶስ አሁንም መካከለኛ እንደ ሆነ ምስክርነቱን የሰጠው ‹‹እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑ ብዙ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል›› በሚለው መልእክቱ ላይ ነው፡፡ (ዕብራውያን 7÷23-25)፡፡

ይህንን ጥቅስ መነሻ በማድረግ፡- ‹‹… ክርስቶስ ያን የካህናቱን ድካምና ሞት አስወግዷልና <u>ስለ እነርሱ ሊያማልድ ማለት</u> ድካሙን መስዋዕቱን አስቀርቶ <u>ለነርሱ ፈርዶላቸዋልና</u>…›› የሚሉት ጸሐፊ ‹‹ስለዚህ ካህናቱ ዛሬ የፍየልና የበግ የጥጃ ደም ሳይሆን ይዘው የሚቀርቡት የክርቶስን ደምና ሥጋ ነው›› በማለት ‹‹ካህናት›› የተባሉት በዚህ ዘመን አሉ ከሚባሉት ካህናት ጋር ለማገናኘት ከመሞከራቸውም ሌላ፤

> ‹ይማልዳልና› ያለው ‹ይፈርዳል ድካማቸውን አስቀርቷል የበጎችና የፍየሎች ደም ተወግዶ በደሙ ነጽተናል› የሚል ፍቺ ያለው ነው፡፡ ተርጕሙ እነርሱ እንደሚሉት ይሁን እንኳ ቢባል እነዛ ካህናት ሞተዋል አልፈዋል፡፡ <u>ስለ እነርሱ</u> በማለት መጽሐፍ ነግሮናል፡፡ ሁሌ ለሞቱት ለእነዚህ የብሉይ ኪዳን ካህናት የለምንላቸዋል የሚል ፍቺ ሊሰጥ ነው፡፡ ታዲያ የጌታ ማዳኑ አንድ ጊዜ ፈጽሞ አደረገው ማለቱን ሁሉ ከንቱ ያደርገዋል፡፡ ፈጽሞ ከጌታ አሠራር ጋር የማይገናኝ ፍቺ ይሆናል ገና <u>ስላለፈው ሊያውም ብሉይ ኪዳን ይለምናል</u> ብሎ የሚሰጠው ፍቺ ፈጹም ስሕተትና ማስተዋል የጎደለው መሆኑን ያመለክተናል

በማለት መጽሐፉን ተገን በማድረግ ከመጽፉ ሐሳብ የራቀ የራሳቸውን ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡[16] በዚህ ሐሳብ ውስጥ ደግሞ ከዚህ በታች ያሉትን ነገሮች እንመለከታለን፤

- ‹‹ስለ እነርሱ ሲያማልድ…›› የሚለውን ‹‹ለነርሱ ፈርዶላቸዋልና›› የሚል ትርጕም የሠሩለት በምን መነሻ እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ የቤተ ክርስቲያቱ ሊቃውንት ባዘጋጁት የአንድምታ ተርጓሜም ሆነ በሌሎች ሥራዎች ወስጥ እንዲህ ያለ ትርጕም ተነቦ አያውቀም፡፡ ጸሐፊው እንዲህ ያደረጉት ምልጃ የሚለውን ቃል ከክርስቶስ ጋር በተያያዘ ያለ ትርጕሙ ትርጕም በመስጠት ቃሉን እነርሱ

[16] አሐዱ አስረስ (ዲያቆን)፣ *ኢየሱስ ፈራጅ ወይስ አማላጅ?* (መስከረም - ጥቅምት 1997 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 48-50፡፡

ለወደዱት አካል ለመስጠት ከመፈለግ የመጣ ጭንቀት መሆኑ ይታወቃል።

- ምንም እንኳ መጽሐፍ ቀዱስ ‹‹ስለ እነርሱ**ም**›› ቢልም፤ ጸሐፊው ግን ‹‹ስለ እነርሱ›› ብለው ያሰፈሩት ሐሳብ አንዱ ችግር ነው። ሐዋርያው ‹‹ስለ እነርሱም›› ካለ በኋላ የክርስቶስ የመካከለኝነት ሥራ ‹‹እነርሱ›› ለተባሉትና ቀደም ሲል ለነበሩት ካህናት ብቻ ሳይሆን ገደብ የሌለው መሆኑን ‹‹ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል›› በማለት ሐሳቡን የተሻለ ግልጽ ያደርገዋል።

6. ለክርስቶስ መካከለኝነት ሌላው ምስክር ሐዋርያው ዮሐንስ ነው፤ እርሱም እንዲህ ሲል ጽፏል፡- ‹‹ልጆቼ ሆይ÷ ኀጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኀጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኀጢአታችን ማስተስሪያ ነው÷ ለኀጢአታችን ብቻ አይደለም÷ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኀጢአት እንጂ›› (1ኛ ዮሐንስ 2÷1-2)።

ክርስቶስ አማላጅ መሆኑን የሚገልጸውን ይህን መልእክት ለማስተባበል የተኬደበት መንገድ መጽሐፉን የመሰረዝና የመደለዝ ሥራ መሥራት ነው። በዚህም መንገድ ሲኬድ ‹‹ጠበቃ››[17] የሚለውን ጸራቅሊጦስ በሚል

[17] አሁን እጆቻችን ባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ‹‹ጠበቃ›› በሚል የተቀመጠው ምንባብ በ1879 በታተመው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ላይ ‹‹ልጆቼ ሆይ ይህቺን ነገር እጽፍላችኋለሁ ኀጢአት እንዳሠሩ። ከላንተም ማንም ኀጢአት ቢሠራ ከአብ ዘንድ <u>አማላጅ አለነ</u> የሱስ

በማስቀመጥና ጳራቅሊጦስ የተባለው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው በሚል መልእክቱን ከክርስቶስ ጋር የማይገናኝ በማስመሰል ማስፈር ነው። ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ አማላጅ ነው የሚለው ትምህርት አንዳንዶች ለሚያስተምሩት የተሳሳተ ትምህርት ስላልተመቻቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ‹‹እነዚህ ወገኖች ከቀናው መንገድ ወጥተው ትምህርተ ሥላሴን በትምህርተ ሰባልዮስ፣ ትምህርተ ሥጋዌን በትምህርተ አውጣኪ ለመተካት ምን አነሣሣቸው? ተብሎ ቢጠየቅ፣ እነዚህን ኑፋቄዎች አምነውባቸው ወይም ለመቀበል ፈልገው እንዳልሆነ ይታወቃል። ዋናው መነሻ ምክንያታቸው ግን ስለ ክርስቶስ መካከለኛነት የሚሰጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከሁለት አቅጣጫ የሚፈጠርባቸው ሥጋት ነው። ይኸውም፡- ክርስቶስን ዛሬም መካከለኛ ነው ማለት በአምላክነት ክብር (ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ) የሚያሳንሰው መስሎ ይሰማቸዋል። ክርስቶስን መካከለኛ ካደረጉ በእርሱ ስፍራ ያቆሟቸው <መካከለኞች> ቦታ አይኖራቸውም፣ ስለ እነርሱም መካከለኛነት የሚያስተምሩት ትምህርትና የሚታመነው ሁሉ ዋጋ ያጣል››።[18]

መጽሐፉ አማላጅ የሚለውን ጳራቅሊጦስ በሚለው ለመሸፈን ይሞክሩ እንጂ የኀጢአታችን ማስተሰሪያው ክርስቶስ መሆኑንና ይህም ለዓለሙ ሁሉ የሚተርፍ እንደ ሆነ በግልጽ መስክረዋል። ‹‹<ጳራቅሊጦስ> አለን የሚለውን

ክርስቶስ ጻድቅ። እርሱም የኀጢአታችን መታረቅ ነው ግን ስለ ኀጢአታችን ብቻ አይደለም ስለ ዓለሙ ሁሉ ኀጢአት እንጂ›› በሚል ነው ሰፍሮ የነበረው።

[18] "ኖኅተ ብርሃን" መስከረም 2002 ዓመተ ምሕረት ገጽ 13።

ንባብ በመጠቀም የኢየሱስ ክርስቶስን ጠበቃነቱን ለማስካድ የሚሞክሩ አሉ። በመሠረቱ ጸራቅሊጦስ የሚለው ቃል ፖራክሊተስ የሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ ትክክለኛ ትርጉሙም አማላጅ፣ አጽናኝ፣ ጠበቃ ማለት ነው››።[19]

❖❖❖

‹‹መምህር›› ዘበነ ለማ ክርስቶስ አማላጅ እንደ ሆነ ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ እንደማይገኝለት አስመስለው የተናገሩትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናዘብ ንግግራቸው ምን ያህል እውነትነት አለው የሚለው ቀደም ሲል ቀርቧል። አሁን ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወጣ በማለት ቤተ ክርስቲያኒቱ የእኔ የምትላቸው የተለያዩ መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ አማላጅነት የሚሉት የሚከተለውን ይመስላል።

የኢየሱስ ምልጃ በአዋልድ እና በሌሎች መጻሕፍት[20]

ከዚህ በታች ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በክርስቶስ ምልጃ ላይ የያዙትን እውነት ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል። እነዚህ መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ምልጃ በተለየ ሁኔታ የሚያስነብቡት ነገር ባይኖርም ከሌሎች ትምህርቶች ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን ነው ለማሳየት የተሞከረው። መጻሕፍቱ የሚያቀርቡት ትምህርት የመጨረሻ ባለ ሥልጣን የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የሚተካና የሚያጸድቅ ነው ማለት እንዳልሆነ ግን መታወቅ አለበት። መጻሕፍቱን የጻፏቸው አባቶች የተገኙት መጽሐፍ ቅዱስን

[19] "የአዲስ ኪዳን መካከለኛ" አሳታሚ BGNLJ ገጽ 26።

[20] በዚህ ርዕስ ስር የሰፈሩት ነጥቦች የተወሰዱት ‹‹ኢየሱስ፤ እውነተኛ አማላጅ፣ ጻድቅ ፈራጅ›› ከተሰኘውና ለሁለተኛ ዕትም ከተዘጋጀው መጽሐፍ ነው።

አንብበውና ተምረው ሲሆን የራሳቸውን መጻሕፍት ያዘጋጁትም መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ አባቶች ሰዎች እንደ መሆናቸው መጠን በሕይወታቸው መውደቅ መነሣት ሊከሠት የሚችልበት ብዙ አጋጣሚ አለ፡፡ ይህም በትምህርታቸው (በስብከታቸው) እና በጽሑፍ ሥራዎቻቸው ላይ ሊገለጥ ይችላልና ትምህርታቸው በቃለ እግዚአብሔር ተፈትሾ ጤናማውን ተቀብሎ ማስተማር ተገቢ እንደ ሆነው ሁሉ ትክክል ያልሆነውን ትክክል አለመሆኑ ሊገለጽ ይገባል፡፡

እነዚህ መጻሕፍት ችግር ያለባቸው ከሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ እነሱን ለማስረጃነት ማቅረብ ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ቢነሣ÷ አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ትምህርት ላለመቀበል ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ፣ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስን መናፍቃን ለራሳቸው ትምህርት እንዲመች አድርገው የበረዙትና የከለሱት በመሆኑ ይህ ጥቅስ በቤተ ክርስቲያናችን አባቶች እንዲህ ተብሎ ተብራርቷል›› የሚል እና ‹‹የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት እንዲህ የሚል አይደለም›› የሚል በመሆኑ ‹‹መናፍቃን›› የተባሉት ሰዎች ሊያገኟቸው ከማይችሏቸውና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያዘጋጇቸው ናቸው ከሚባሉት መጻሕፍት ጠቅሶ ሐሳቡን ማቅረብ ግድ በማለቱ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ቀደም ያሉትን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትም ብቻ ሳይሆን የቅርብ ጊዜ የጽሑፍ ሥራዎችንም ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ የተደረገው ደግሞ በዘመናችን ያሉ አባቶችም ሆኑ ወንድሞች ፊት ለፊት ‹‹ኢየሱስ አያማልድም›› ቢሉም፣ መጽሐፉ ግድ ሲላቸው

ዐውቀውትም ይሁን ሳያውቁት ስለ ኢየሱስ አማላጅነት ምን እንዳስነበቡ ለማሳየት ያህል ነው።

ከመጻሕፍት የተገኙትን ሐሳቦች ቃል በቃል ለማስቀመጥ ጥረት የተደረገ ሲሆን ትኩረት እንዲደረግበት የተፈለገው ክፍል ጐላ ያለ መሥመር ከሥሩ የተደረገበት በዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ነው።

1. <u>ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት</u>

<u>ሃይማኖተ አበው</u>

- ‹‹ሊቀ ካህናት እርሱ <u>ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ</u››።[21]
- ‹‹እንደዚህም ወንጌላዊ ዮሐንስ እኛ ለአባቱ አንድ እንደ ሆነ ልጅ ክብር ያለ ክብሩን አየነ አለ፤ <u>በሥጋ ባሕርይ ግን ሰው ይባላል መሥዋዕትነትን፣ አስታራቂነትን እውነትን ገንዘብን ያደረገ እንደ ሆነ</u> ስለ እርሱ ዮሐንስ እንደተናገረ ታወቀ››።[22]
- ‹‹ዳግመኛ <u>አስታራቂያችን እንደ ሆነ</u> የእኛንም መከራ መቀበል እንዲችል ከኀጢአት በቀር በሥራ ሁሉ እንደ እኛ እንደ ተፈተነ ስለ እርሱ ሲናገር ጳውሎስን እንሰማው››።[23]
- ‹‹ሰው የሆነም ዘመድ ሊሆነን ብቻ አይደለም፤ ፈጽሞ ይቅር አለን ኀጢአታችንን ለማስተሰረይ፤ <u>ከአብ ጋር ለማስታረቅ ሊቀ ካህናትም ይሆነን ዘንድ ወደደ እንጂ</u>፤

[21] አመ ዘሐዋርያት ምዕራፍ 6 ክፍል 1 ቍጥር 23 — አጽንዖት የግል።
[22] ዘነርሳርዮስ ምዕራፍ 35 ክፍል 1 ቍጥር 7 - አጽንዖት የግል።
[23] ዘዮሐንስ ምዕራፍ 52 ክፍል 1 ቍጥር 8 - አጽንዖት የግል።

ስለዚህም ሰዎች ሊመስላቸው ይገባል ባለው ነገሩ ላይ ጨምሮ በሁሉ ዐዛኝ የሕዝቡንም ኀጢአት ለማስተሰረይ በእግዚአብሔር ዘንድ <u>የታመነ አስታራቂ ይሆናቸው ዘንድ ነው አለ</u>። ባሕርያችንን ስለ ተዋሐደ ሰው የመሆኑን ነገር ያስተምረን ዘንድ ይኽን ተናገረ። ሰው ለመሆን ያበቃው <u>ለማስታረቅ ኀጢአትን ለማስተሰረይ ብቻ ነው እንጂ</u> ሌላ ምክንያት የለውም፤ ከእርሱ በቀር ራሱ ብቻውን ኀጢአት ማስተሰረይ የሚቻለው <u>የታመነ አስታራቂ ማን ነው? ለማስታረቅ ኀጢአትን ለማስተሰረይ ያቀረበው መሥዋዕትስ ምንድን ነው? መሥዋዕት ለመሆን የነሣው ሥጋው ብቻ ነው እንጂ</u>››።[24]

➪ ‹‹ከዚህም በኋላ የምናምንበትን <u>አስታራቂ ሐዋርያ</u> እርሱን አብነት አድርጉት አለ አብ ከወዲያ ዓለም ወደዚህ ዓለም ስለ ላከው ሐዋርያ አለው፤ ስለ አመንበት በጎ ሥራ ለመሥራት የምንቀና፤ ደግ ወገን አድርጎ ገንዘብ አደረገን <u>ለእኛ ማልዶልናልና የምናምንበት ሊቀ ካህናት (አስታራቂ) አለው</u>››።[25]

➪ ‹‹በመስቀል በተሰቀለ በሥጋው ብቻ ወደ እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደ አቀረበን <u>በእርሱና በእኛ መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ እንደ አጠፋ የክርስቶስ ነገር ሐዋርያት ተናገረ</u> አለ። ወደ እርሱ አቀረበን ያለው ርቀን መኖራችንን ያስረዳል የሰው ባሕርይ ከእግዚአብሔር

[24] ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕራፍ 63 ክፍል 2 ቍጥር 13-14 - አጽንዖት የግል።

[25] ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕራፍ 63 ክፍል 2 ቍጥር 26 - አጽንዖት የግል።

ተለይቶ ነበርና በደጋጎች አበው በነቢያት በኦሪት ከእነርሱ አስቀድሞ በነበረው ዘመን ሁሉ አዳምም ከበደል ጀምሮ ከእነዚህ ሁሉ ወደ እርሱ ሊያቀርበን ማንም ማን አልቻለም ነበረና››::[26]

- ‹‹እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስማማ ክርስቶስ ሰው ሆነ <u>ሁለቱንም አስታረቃቸው</u>››::[27]
- ‹‹ለሰው የሚገባን የተፈተነባቸውን ሥራዎችም ገንዘብ ባደረገ ጊዜ፤ ዛሬ እኛ እሱን አብነት አድርገን መከራ እንቀበል ዘንድ ነው፤ <u>በመለኮቱም ኀጢአትን ሁሉ የሚያጠፋ እሱ ሰው በመሆኑ አስታራቂ ሆነ</u>፤ እንደ አገልጋይም ሆኖ ንጹሕ ሥጋውን <u>ለእግዚአብሔር አብ ስለ እኛ ሠዋ</u>፤ በመለኮቱ የማይታመም ሲሆን ራሱን የተወደደ መሥዋዕት፤ ያማረ ዕጣን አድርጎ አቀረበ››::[28]
- ‹‹ዛሬስ በምን ሥራ በምን ነገር በእግዚአብሔር ፊት ተገለጠ፤ አምላክ ቃል እንደ እኛ ሰው ሆኖ በዐዲስ ሥራ ተገለጠ፡፡ ዓለም ሳይፈጠር ሥጋንም ሳይዋሐድ በመለኮቱ በአብ ዘንድ ህልው ሲሆን <u>ዛሬ ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት በእኛ ባሕርይ በአስታራቂነት ተገለጠ</u>››::[29]

---

[26] ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕራፍ 68 ክፍል 21 ቍጥር 16-17 - አጽንዖት የግል፡፡

[27] ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕራፍ 68 ክፍል 22 ቍጥር 21 - አጽንዖት የግል፡፡

[28] ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕራፍ 79 ክፍል 50 ቍጥር 68 - አጽንዖት የግል፡፡

[29] ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕራፍ 79 ክፍል 50 ቍጥር 72 - አጽንዖት ግል፡፡

➪ ‹‹ሰው ከሆነ በኋላ ብእሲ መሲሕ ኢየሱስ ታቦት <u>አስታራቂ</u> ለሙታን በሙር ከሙታን ወገን ለሚነሣም በሙር የምእመናን ገገር ፈጣሪ ተባለ››።[30]

➪ ‹‹ሁሉን የፈጠረ አምላካችን ከድንግል መወለድን፤ በዐጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰንን፤ ዘመን የሚቈጠርለት መሆንን መሰቀልን፤ በከርሰ መቃብር ማደርን፣ ወደ ሲኦል መውረድን በወደደ ጊዜ በፍዳ ተይዘን ስለ ነበር በእነዚህ ሁሉ የተቤዠን አይደለምን፤ <u>ራሱ ከታረቀን በኋላ አዳነን</u>››።[31]

➪ ‹‹የነጎድጓድ ልጅ አንድነት ሦስትነትን የተናገረ ዮሐንስ እንደ አስተማረ፤ *ቃል ሥጋ* ሆነ በእኛም ዐደረ፤ በአምላክነት በሰውነት ሥራ ሁሉ ፍጹም የሆነ ጌትነቱን አየን ጌትነቱም በአባቱ እሪና እንዳለ እንደ አንድ ልጅ ጌትነት ከአባቱ ጋር እኩል ትክክል ነው፤ ቤዛ ሆኖ መስጠት ኀጢአትን ማስተሰረይ፤ <u>አስታራቂነት ገንዘቡ ነው ብሎ የተናገረው ቃል ፍጹም ትምህርቱም ረቂቅ ስለ ሆነ ወልደ ነጎድጓድ ተብሏልና</u>››።[32]

➪ ‹‹*ሥጋው* በመገነዙም ፈርሶ፤ በስብሶ መቅረት ጠፋ፤ የትንሣኤ በሙር ሆኖ ተገለጠ፤ የትሩፋት መምህርም ሆኖ በዚህ ዓለም ሃይማኖትን አስተማረ፤ ለሰው መንግሥተ ሰማያትን አስተማረ ልጅነትን ለመስጠት <u>በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አስታራቂ ሆነ</u>፤ ሰውን ሁሉ ለማዳን አንድ ልጁን የሰጠው አብን እናመሰግነው፤

[30] ዘቂርሎስ ምዕራፍ 81 ክፍል 52 ቍጥር 8 - አጽንዖት የግል።
[31] ዘብንያም ምዕራፍ 89 ክፍል 1 ቍጥር 25 - አጽንዖት የግል።
[32] ዘሱኑትዩ ምዕራፍ 110 ክፍል 2 ቍጥር 26 - አጽንዖት የግል።

ዳግመኛ በእኛ ዐድሮ የሚያድነን፤ ከእግዚአብሔር ጋርም አንድ የምንሆንበትን ሀብት የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስንም እናመሰግነው››::[33]

መጽሐፈ ዲድስቅልያ

- ‹‹ ‹አባት ሆይ! የማያውቁትን ያደርጋሉና ይቅር በላቸው› ተብሎ በወንጌል እንደ ተጻፈ መድኀኒታችን ወደ አባቱ ለምኗልና››::[34]
- ‹‹ነገር ግን ጌታችን ያስተምረናል፣ እኛን እስራኤልን ያዳነን እግዚአብሔር ያዋርድህ ይገሥጽህ ብሎ ረገመው ገሠፀውም፤ እናንተ ቀድሞ ተሰብስባችሁ ሳላችሁ ሃይማኖታችሁ እንዳይደክም ስለ እናንተ አብን ለመንኩት ብሏልና››::[35]
- ‹‹ከአብ ጋራ አስታራቂያችን የሚሆን እርሱ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋራ አስታረቀ››::[36]

ድርሳነ ዮሐንስ አፈወርቅ

- ‹‹ይተነብል[37] ያለው ስለ ሰውነቱ እንደ ሆነ ወዳጄ አወቅህ ተረዳህን? ሊቀ ካህናት ቢሆን ያን ጊዜ ተንበለ[38] ተባለ››

---

[33] ቃለ ግዝት ምዕራፍ 117 ክፍል 1 ቍጥር 7 - አጽንዖት የግል።

[34] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ዲድስቅልያ (2004) አንቀጽ 6 ቍጥር 6 - አጽንዖት የግል።

[35] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ዲድስቅልያ (2004) አንቀጽ 31 ቍጥር 43 - አጽንዖት የግል።

[36] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ዲድስቅልያ (2004) አንቀጽ 33 ቍጥር 22 - አጽንዖት የግል።

[37] ‹‹ተንብሎት፤ ሎት፤ (ተንበለ፣ ይተንብል፣ ይተንብል፣ ነበ፣ ነበየ፣ ብህለ)፤ መለመን፣ መጸለይ፣ መማለድ፣ ማማለድ፣ ማላጅ፣ አማላጅ መሆን፣ ዕርቅ ፍቅር ይቅርታ መፈለግ ማረኝ ማለት...›› (ኪዳነ ወልድ

ጳውሎስ ተንበለ ያለው ሊቀ ካህናት ለልማዱ ይለምናልና[39] ስለዚህ ነው ማለት ነው። (አንድም) <u>ሊቀ ካህናት ነውና ይለምናል ማለት ነው</u>። (አንድም) ይተነብል ያለው ሊቀ ካህናት እንደ ሆነ መናገር ነው›››።[40]

➪ ‹‹<u>ያለ ወልድ አስታራቂነት ምንም ምን ማቅረብ አይቻልም</u>›››።[41]

<u>መጽሐፈ ሰዓታት</u>

➪ ‹‹አብ ሆይ ስለ ኢየሱስ ርዳን <u>ክርስቶስ ወደቸር አባትህ አማልደን</u> የአብና የወልድ መንፈስ አጽናናን›››።[42]

➪ ‹‹እግዚአብሔር በተከላት የምስክር ድንኳን ለቅዱሳን <u>የሚቆምላቸው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው</u>›››።[43]

ክፍሌ (አለቃ) *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ* (1948) ገጽ 900)።

[38] ‹‹ትንባሌ = ልመና፣ ተንበል = ልመና፣ ተንባል = ለማኝ (ልመና)›› (አፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ) - *መምህረ ግእዝ ወቅኔ፣ ሀገረ-መጻሕፍት፣ ሰዋስው ግእዝ ወዐማርኛ* (1988) ገጽ 196።

[39] የክርስቶስን አማላጅነት መቀበል የሚቸግራቸው ሰዎች፤ ‹‹ኢየሱስ አማላጅ አይደለም›› የሚለውን ለመቃወም ከሚያደርጉት ሙከራ ውስጥ አንዱ÷ ‹የሊቀ ካህናት አገልግሎት መሥዋዕት ማቅረብ እንጂ የምልጃ አገልግሎት አይደለም› የሚለው መሆኑን በተለይ በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን በሚንሸራሸሩ ሐሳቦች ውስጥ ይታያል። በዚህ በዮሐንስ አፈወርቅ ሐሳብ ውስጥ ግን የሊቀ ካህኑ አንዱ ሥራ መለመን መሆኑና ኢየሱስም ያንን ማድረጉን ያሳያል።

[40] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ *ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ* (1989) 13ኛ ድርሳን ቁጥር 130-132 - አጽንዖት የግል።

[41] የቀደመው መጽሐፍ፣ 33ኛ ድርሳን ቁጥር 218 - አጽንዖት የግል።

[42] ሰዓታት ስብሐተ ፍቁር ዘአምላክ ገጽ 222 - አጽንዖት የግል።

[43] መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ ገጽ 122 - አጽንዖት የግል።

አርጋኖን - የእመቤታችን ምስጋና

➪ ‹‹[ሰይጣን] ቢያጣላኝም በሰማይ የሚኖር ተስፋ አለኝ፤ <u>ሥጋሽን የለበሰ ወልድ በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ የሚጣላልኝ የሚከራከርልኝ[44] አለና</u>...››::[45]

መጽሐፈ ቅዳሴ

➪ ‹‹ስለ እኔ በቀራንዮ የፈሰሰ ንጹሕ የሚሆን የመሢሕም ደም እነሆ <u>ስለ እኔ ይጮኻል</u>፣ ይህ የሚናገር ደም የእኔን አገልጋይህን <u>ኀጢአት የሚያስተሠርይ ይሁን</u>››::[46]

➪ ‹‹ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ቀና ብሎ አየ፤ <u>የወለደውንም ማለደ</u>:: ደቀ መዛሙርቱንም ከክፉው ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ ዐደራ አስጠበቀ››::[47]

➪ ‹‹ዳግመኛ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ የተነሣ ምንም ምን ሕፀፅ እንደሌለበት እናምናለን:: በእውነት ሰው የሆነ

---

[44] ‹‹እሱ ቢያጸድቅ ማን ይኰንነናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ:: በአብ ዕሪና ይኖራል ስለ እኛ ይከራከራል:: መከራከርስ የለም ስለ እኛ በዕለተ ዐርብ ባደረገው ተልእኮ ፍጹም ዋጋችንን የምናገኝ ስለ ሆነ›› እንደ ሆነ የሰፈረው? (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ግንቦት 1988) ገጽ 70:: *መሓሪ ትርፌ* (ሊቀ ሊቃውንት)፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ጥቅምት 23 1948) ገጽ 100::)

[45] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 291:: አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 305-306 - አጽንዖት የግል::

[46] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ፣ ቅዳሴ ሐዋርያት ቁጥር 106::

[47] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ፣ ቅዳሴ ማርያም ቁጥር 103 - አጽንዖት የግል::

የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ፣ የአብ ሊቀ ካህናት የሚሆን እርሱ <u>የሰውን ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ</u>››::[48]

➪ ‹‹ያልተሠራ ልብስ ያልተፈተለ ቀሚስ <u>ወደ አባቱ ለመድረስ ጎዳና፤ ወደ ወለደው ለመግባት የሚሆን በር</u>፣ የተገለጸ ወርቅና የተገኘ ዕንቍ ነው። የበዛ ምናን፣ እጽፍ ድርብ የሆነ መክሊት ዱቄትን የቻለው እርሾ አልጫ የሆነውን ያጣፈጠውን ጨው››::[49]

<u>መጽሐፈ ዚቅ</u>

➪ ‹‹ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የእኔ ስለሆኑት ምሕረትን <u>ወደምለምንበት</u> ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ››::[50]

<u>ውዳሴ ማርያም</u>

➪ ‹‹<u>ወኮነ ዐራቂ ለዐዲስ ኪዳን</u>፤[51] ለወንጌል ሊቀ ካህናት፤ <u>ለመንግሥተ ሰማያት አስታራቂ ሆነ</u>››::[52]

---

[48] ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ፣ መጽሐፈ ቅዳሴ በሥርዓተ ክፍሉ ቍጥር 43 - አጽንዖት የግል።

[49] ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ፣ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቍጥር 44 - አጽንዖት የግል።

[50] መጽሐፈ ዚቅ ዘሰኔ ሚካኤል ገጽ 188/189 (የ1986 እትም) - አጽንዖት የግል።

[51] ‹‹የዐዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆነ››

[52] ትንሣኤ የመጻሕፍት ማኅተሚያ ድርጅት፣ ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው (ዐዲስ አበባ፣ 1983) ገጽ 188 - አጽንዖት የግል።

➪ ‹‹ሰውን የሚወድ ሰው የሚወደው እርሱ የኛን ሞት ነሥቶ የእርሱን ሕይወት ለኛ ሰጥቶ ካባቱ ጋራ አስታረቀን››።[53]

➪ ‹‹በመካከል ሆኖ በመስቀሉ አስታረቀን፤ ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ[54] እንዲል››።[55]

መጽሐፈ ምሥጢር

➪ ‹‹ስለ ደቀ መዛሙርቱ እየማለደ አንተ አባቴ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እንዳለሁ እነርሱም እንደ እኛ በእኛ አንድ ይሁኑ፤ አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ሁሉ ያምን ዘንድ አለ››።[56]

➪ ‹‹... [ደሙን] ያፈሰሱትን እየተካሰሰ በማመን ስለሚቀበሉትም ኀጢአታቸውን ይቅር እያለ ወደ አባቱ የሚጮኽ የሚናገር የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በርሷ [በኢየሩሳሌም] ላይ ፈሰሰ››።[57]

---

[53] የቀደመው መጽሐፍ፣ ገጽ 151 - አጽንዖት የግል።

[54] በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ ሰላምን አደረገ ማለት ነው።

[55] ትንሣኤ የመጻሕፍት ማኅተሚያ ድርጅት፣ *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ 1983) ገጽ 156 - አጽንዖት የግል።

[56] ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (አባ)፣ ተርጓሚ ሕሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ *መጽሐፈ ምሥጢር* (መጋቢት 2001) ምዕራፍ 2 ቍጥር 21 - አጽንዖት የግል።

[57] ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (አባ)፣ ተርጓሚ ሕሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ *መጽሐፈ ምሥጢር* (መጋቢት 2001) ምዕራፍ 5 ቍጥር 26 - አጽንዖት የግል።

የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው

- ‹‹የምንመካም በመታረቃችን ብቻ አይደለም ከእግዚአብሔር ዘንድ አስታራቂያችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ነው እንጂ››::[58]
- ‹‹እሱ ቢያጸድቅ ማን ይኰንነናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተ ከመ·ታንም ተለይቶ ተነሣ:: በአብ ዕሪና[59] ይኖራል ስለ እኛ ይከራከራል:: መከራከርስ የለም ስለ እኛ በዕለተ ዐርብ ባደረገው ተልእኮ ፍጹም ዋጋችንን የምናገኝ ስለ ሆነ››::[60]
- ‹‹በሱ አስታራቂነት ወደ እግዚአብሔር የቀረቡትን ማዳን ይቻለዋል:: ፈጽሞ ሕያው ነውና:: ተንበለ[61] ሲል፤ አንድም በቁመ· በዕለተ ዐርብ ባደረገው ተልእኮ እስከ ምጽአት ድረስ ሲያድንበት የሚኖር ስለ ሆነ››::[62]

---

[58] ትንሣኤ ዘገባኤ ማተሚያ ቤት፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ግንቦት 1988 - ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ) ገጽ 52:: መሓሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ጥቅምት 23 1948) ገጽ 73::

[59] ዕሪና ማለት እኩል ወይም መተካከል ማለት ነው::

[60] ትንሣኤ ዘገባኤ ማተሚያ ቤት፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ግንቦት 1988) ገጽ 70:: መሓሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ጥቅምት 23 1948) ገጽ 100::

[61] ተንበለ ‹‹መለመን፣ መጸለይ፣ መማለድ፣ ማማለድ፣ ማላጅ፣ አማላጅ መሆን፣ ዕርቅ ፍቅር ይቅርታ መፈለግ ማረኝ ማርልኝ ማለት›› (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ) *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ* (1948) ገጽ 900)::

[62] ትንሣኤ ዘገባኤ ማተሚያ ቤት፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ግንቦት 1988) ገጽ 434:: መሓሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* (ዐዲስ አበባ፣ ጥቅምት 23 1948) ገጽ 647::

መጽሐፈ ሄኖክ[63]

- ‹‹ከዚህ በኋላ እውነተኛ አስታራቂ ክርስቶስ ጻድቃንን በሚሰበስብበት በመንግሥተ ሰማይ ይገለጣል››።[64]
- ‹‹አስታራቂ ክርስቶስ በመላእክት ጌታ ፊት ቁሟልና አሰት ነገርም እንደ ጥላ ያልፋል። ቆሞ የሚሠወሩበት ቦታ የለም››።[65]
- ‹‹አስታራቂ ክርስቶስም በነዚያ ወራት በዙፋኑ ይቀመጣል የመላእክት ጌታ ሰጥቶ አክብሮታልና የተሠወረ የጥበብን ነገር ሁሉ ዐስቦ ከሚናገርበት ከአንደበቱ ያወጣል››።[66]
- ‹‹አስታራቂ ክርስቶስ በመላእክት ጌታ በአብ ፊት በተገለጠ ጊዜ ጠላቶቹ ጎጥኣን ከመንግሥተ ሰማይ ይጠፉ ዘንድ አላቸው››።[67]
- ‹‹በነገር ሁሉ እየተራቀቁ ሕይወት በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኙ ያመሰግኑታል። የመላእክት አብ አስታራቂ ክርስቶስን በጌትነቱ ዙፋን አስቀመጠው››።[68]

---

[63] በ1980 ዓመተ ምሕረት የታተመው ሰማንያ አሐዱ በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ብቻ ለ10 ጊዜ ያህል የኢየሱስ አስታራቂነት የተጠቀሰ ቢሆንም በ2000 ዓመተ ምሕረት በታተመው ሰማንያ አሐዱ ግን ሁሉንም ለማጥፋት ጥረት ተደርጓል (ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ *ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን* (ጥር 2010 - ሦስተኛ ዕትም) ገጽ 136-137)።

[64] መጽሐፈ ሄኖክ 14÷19 - የ1980 ዕትም - አጽንዖት የግል።

[65] መጽሐፈ ሄኖክ 13÷19 - የ1980 ዕትም - አጽንዖት የግል።

[66] መጽሐፈ ሄኖክ 13÷31 - የ1980 ዕትም - አጽንዖት የግል።

[67] መጽሐፈ ሄኖክ 14÷11 - የ1980 እትም - አጽንዖት የግል።

[68] መጽሐፈ ሄኖክ 17÷12 - የ1980 እትም - አጽንዖት የግል።

2. <u>የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከጻፉት</u>

<u>ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ</u>

➪ ‹‹<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን እሱ ታርቆ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አስታርቆ</u> በመስቀሉም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ ካፈረሰው በኋላ ለሰው ልጆች[69] የባለሟልነትን÷ የማስታረቅን÷ የማማለድን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል››::[70]

<u>ትምህርተ ክርስትና</u>

➪ ‹‹በአንድ በእግዚአብሔር አብ እንደምናምን ሁሉ በአንድ ጌታ በአንዱ አዳኝ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤ አዳኛችን እርሱ አንድ ጌታ ነውና፡፡ ሁላችን የዳንነው በዚህ የአብ አንድያ የባሕርይ ልጅ በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ነው፤ <u>አሁንም ወደ አብ የምንቀርበው አስታራቂያችን በሆነው በዚሁ ጌታ በኢየሱስ</u>

---

[69] ጸሐፊው፤ የሰው ልጅ በክርስቶስ በኩል የተደረገውን የማስታረቅ ሥራ ካስቀመጡ በኋላ ለሰው ልጆች ተሰጠ የሚሉት የማማለድ ሥራ ምን እንደ ሆነ ግልጽ አላደረጉም፡፡ በክርስቶስ አንድ ጊዜ የተሠራው የማስታረቅ ሥራ እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ሌላ አስታራቂ አስፈላጊ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ከራሱም ጋር ከእግዚአብሔርም ጋር እንዳስታረቀን ካስቀመጠው ውጪ ሌላ የማስታረቅ ሥራ ሊሠራ የሚችል እንዳለ አያስተምርምና፡፡

[70] አያሌው ታምሩ (አለቃ)፤ *ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ* (ዐዲስ አበባ፤ ሐምሌ 1979) ገጽ 26-27 - አጽንዖት የግል፡፡

<u>ክርስቶስ አማካይነት ነው</u>። እርሱ እውነተኛ መንገድ ነው››።[71]

<u>ጎሐ ጽባሕ</u>

➪ **‹‹ቀድሞ እኛ ሁላችን በኀጢአታችን ብዛት ብዙ ዘመን ከእግዚአብሔር ፊት ርቀን ስንኖር <u>እርሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱና በእኛ መካከል ሆኖ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቈርሶ አስታርቆናል</u>። በእርሱም አስታራቂነት ወደ መጋረጃው ውስጥ ገብተን በእግዚአብሔር ፊት በባለሟልነት ለመቆም ተፈቅዶልናል፤ ስለዚህ <u>ክብራችንና ደስታችን ትልቅ ነው</u>። - ዕብራውያን 6÷18-20፤ 10÷19፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2÷10፤ ኤፌሶን 2÷19››።**[72]

<u>ኰኵሐ ሃይማኖት</u>

➪ **የኰኵሐ ሃይማኖት አዘጋጅ አለቃ ታየን ጠቅሰው ያሰፈሩት፤ ‹‹የቀደሙ አባቶቻችን በኀጢአት ከተሰነካከሉ በኋላ በአዳምና በልጆቹ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው በበጎ ሥራቸው የታወቁ ኖኅና አብርሃም ሌሎችም በአዳም መርገም ተያዙ እንጂ በሥራቸው ሊድኑ አልቻሉምና የራሳቸው የራሳችን ሥራ ይበቃናል የምትሉ ሰዎች ከክርስቶስ ጸጋ እንዳትወድቁ <u>ያለ ክርስቶስ አስታራቂነት አብርሃም በሃይማኖቱ ኢዮብ በትእግስቱ ሊድኑ</u>**

---

[71] መልከ ጼዴቅ (አባ)፤ *ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ* (ዐዲስ አበባ፤ 1984) ገጽ 32 - አጽንዖት የግል።

[72] ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፤ *ጎሐ ጽባሕ* (1919) ገጽ 9 — አጽንዖት የግል።

አለመቻላቸውን ከብሉይ ከዐዲስ መርምራችሁ ተረዱ...››::[73]

ሁሉም ሁሉን ይወቅ

➪ ‹‹ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ÷ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ወልደ ማርያም ሥግው÷ ሰውን ለማዳን ሥጋ ለብሶ÷ ሥጋ በመልበሱ ሰው በመሆኑ÷ ለማኝም÷ አስታራቂም÷ ታራቂም÷ አማላጅም÷ ተማላጁም ነው:: በዚህም በመለኮቱ በሥልጣኑ ከአብ ከባሕርይ አባቱ÷ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ አያንስም::... እንደ አምላክነቱ ይማለዳል÷ እንደ ሰውነቱ ይማልዳል÷ ይለምናል:: ወደ አብ ወደ አባቱም ይጸልያል÷ ጸልዮማል÷ በጥንተ አብሶ ከአዳም የመጣውን ኀጢአታችን በመስቀሉ ደምስሷል:: ለእያንዳንዳችን አሁንም ይከራከራል::››[74]

ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት

➪ ‹‹ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን መሥዋዕት በመሆኑ እውነተኛ አስታራቂያችን ሆኗል:: ቤተ ክርስቲያንም በእርሱ ስም÷ በእርሱ መሥዋዕት የማስታረቁን ሥራ እርሱ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ በኃላፊነት እንድትሠራ ታዛለች (2ኛ ቆሮንቶስ 5÷18-21፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11÷23-26፤ ማቴዎስ 28÷19-20):: ስለዚህ ነው

[73] አድማሱ ጅንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ *ኦሪት ሃይማኖት* (ዐዲስ አበባ፣ የካቲት 1989) ገጽ 184 - አጽንዖት የግል::

[74] አለማየሁ ሞገስ ደርሶ (ቀደሰ)፣ *ሁሉም ሁሉን ይወቅ* (ዐዲስ አበባ፣ 1987) ገጽ 54፡ - አጽንዖት የግል፡

ክርስቶስ ‹ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘላለሙ ድረስ <u>አስታራቂ ሆነን</u>› ተብሎ የተጻፈው (ሄኖክ 13÷9)።››[75]

➪ ‹‹ክርስቶስ ‹<u>መካከለኛ</u>› የተባለበት አዳምና ልጆቹ ሁሉ <u>በኀጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተው÷ ተለይተውና ርቀው የነበሩትን በማስታረቁና በማቅረቡ ነው</u>። ‹ወኮነ ዐራቂ ለሐዲስ ኪዳን በውኂዘ ደሙ ቅዱስ አንጽሖሙ ለመሃይምናን... በከበረ ደሙ ፈሳሽነት በዓለመ ሥጋ በዓለመ ነፍስ ያሉትን አዳናቸው› አነጻቸው ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር አቀረባቸው (ዕብራውያን 12÷24 እና የእሑድ ውዳሴ ማርያም ትርጕም ተመልከት)። በቅድሚያ እርሱ ራሱ በተዘመዶተ ሥጋ ማለት ሰው በመሆኑ ወደ እኛ ቀርቧል፤ <u>ከእኛም ጋር ታርቋል</u>። እንግዲህ እርሱ ራሱ በሰውነቱ ቀርቦ አቅርቦናል÷ <u>ታርቆ አስታርቆናል</u>... በክርስቶስ የተገኘው ጸጋ ግን ኀጢአትን የሚደመስስ÷ <u>ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ</u>÷ መንግሥተ ሰማያትን የሚያሰጥ ሆኗል። ይህም ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አዳኝ አድርጎ በመስጠቱ የመዳን ጸጋችንን አገኘን››።[76]

---

[75] አበራ በቀለ (ሊቀ ጉባኤ)፣ *ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት* (2008 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 141-142 - አጽንዖት የግል።

[76] የቀደመው መጽሐፍ ገጽ 234 - አጽንዖት የግል።

ክብረ ቅዱሳን

➪ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ ተማላጅ አዳኝ፣ ይቅር ባይ መሆኑን በመካድ እሱን ‹አማላጅ፣ ጠበቃ› ነው ብሎ የሚያምን ሁሉ ይፈረድበታል›› ብለው የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቍጥር 18ን የሚጠቅሱት አባ ገብርኤል መልሰው ደግሞ ‹‹በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአንዳንድ ምዕራፎች ‹ክርስቶስ ሰገደ፣ ጸለየ፣ ለመነ…›› ተብሎ የተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ የደኅንነትን ሥራ ከመፈጸሙ በፊት ስለ እኛና ስለ መላው ዓለም ያደረገውን (የፈጸመውን) <u>የሊቀ ካህናትነትንና የማስታረቅ አገልግሎትን ለመግለጽ ነው</u>፤ … ሰው ሆኖ ወደ ዓለም የመጣበትን <u>የማስታረቅንና የማዳንን ሥራ</u>…›› ለመግለጽ ነው ይላሉ።[77]

መልሕቅ (ክፍል ሁለት)

➪ ‹‹<u>ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ አንድ ጊዜ ባፈሰሰው ደሙ በብሉይም ሆነ በዐዲስ ኪዳን ላሉትና ወደፊትም እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ለሚኖሩት ሰዎች በሙሉ አንድ ጊዜ ማልዶላቸዋል</u>››።[78]

---

[77] ገብርኤል (አባ)፣ *ክብረ ቅዱሳን* (ዐዲስ አበባ፣ 1990) ገጽ 22-23 - አጽንዖት የግል።

[78] ጌታቸው ተረፈ (መምህር)፣ *መልሕቅ* (ክፍል ሁለት) (መስከረም 2010 - 2ኛ እትም) ገጽ 186-187።

ተፋልሶ

➪ **ዮሐንስ አፈወርቅን ጠቅሶ እንዳሰፈረው፡- ‹‹አሁን በራሱ ክብር ቢታይም እስከ አሁን ደረስ ስለ እኛ ማሰቡን አልተወም፤ ልክ እንደ በፊቱ ዛሬም ደረስ ፍቅሩ አልተለወጠም፣ በመሞቱ ሳይረካ ዛሬም ይማልዳል››፡፡**[79]

➪ **ቅዱስ ጎርጎርዮስን ጠቅሶ እንዳሰፈረው፡- ‹‹እነዚያ ሰዎች ስለ እኛ ዘወትር ሊያማልድ ይኖራል የሚለውን አባባል በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል፡፡ እንዴት ያለ ውብ ምስጢር የተሞላበት መልካም ነገር መሰላችሁ፡፡ መማለደ ማለት በሰዎች ዘንድ እንደሚሆነው በቀል የሚፈልግን ሰው መለመንን አያመለክትም፡፡ እንዲህ ቢሆን ኖሮ ውርደትና የሚያሳፍር ነገር በሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ እንደሚማልድ ስለ ሰዎች መለመንንና መካከለኛ መሆንን የሚያመለክት አባባል ነው፡፡ አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ መካከለኛ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡ እርሱ አሁንም ቢሆን እንደ ሰውነቱ (ሰው እንደ መሆኑ) ለድኅነቱ ይለምናል፡፡ በሥግውነቱ (በክርስቶስ) ኃይል እኔን የጸጋ አምላክ እስኪያደርገኝ ድረስ የነሣውን ሥጋ አሁን ድረስ ተዋሕዶታልና››፡፡**[80]

➪ **ቅዱስ ቄርሎስን ጠቅሶ እንዳሰፈረው፡- ‹‹እንዲሁም አሁን (ክርስቶስ) በሥጋ እንደሚሆነ ባናውቀውም ማለትም**

---

[79] ጌታቸው ተረፈ (መምህር)፣ *ተፋልሶ - ክፍል አንድ* (የካቲት 2011) ገጽ 241፡፡

[80] ጌታቸው ተረፈ (መምህር)፣ *ተፋልሶ - ክፍል አንድ* (የካቲት 2011) ገጽ 242፡፡

ከንጢአት በቀር ሰው ቢሆንም እንደኛ የሥጋ መከራ (የለበትም)። በመሆኑም ለእኛ ጠበቃ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። በእርግጥ ይህ ማለት ከአብ ፊት ስለ እኛ አይሰግድም (አይወድቅ አይነሣም)፣ ከፊቱም እንደ ባሪያ አይንበረከክም። እንዲህ ካለው እንደ ባሪያ ከመመልከትና ለመንፈስ የማይገባውን ነገር ከማሰብ ራቁ! አብ ይህን ይፈልጋል ወልድም ይገባል ማለት የማይመስል ነገር ነው። ደግሞም እንዲህ ያለውን ነገር ስለ እግዚአብሔር ማሰብ ትክክል አይደለም። ነገር ግን እንደ ሰው በተቀበለው መከራ እርሱ (ክርስቶስ) እንደ አካላዊ ቃልነቱና እንደ ጠበቃነቱ ይታገስ ዘንድ ይለምናል (ይማልዳል)››።[81]

ሐመረ ተዋሕዶ

➪ ‹‹ቀጣይነት ባለው ግስ ‹ይማልዳል› ‹ሲያማልድ በሕይወት ይኖራል› ወዘተረፈ የሚሉት ጥቅሶች ጌታ የፈጸመው የማዳን ሥራ የማስታረቅ አገልግሎት እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚነሣው ትውልድ ሁሉ የሚሆን መሆኑን የሚያስረዳ ነው››።[82]

ኖኅተ ሃይማኖት

➪ ‹‹...በዕለተ ዓርብ የፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት ዛሬም እኛን ከአብ፣ ከወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ባጭሩ

[81] ጌታቸው ተረፈ (መምህር)፣ *ተፋልሶ - ክፍል አንድ* (የካቲት 2011) ገጽ 242።

[82] ማኅበረ ቅዱሳን፣ *ሐመረ ተዋሕዶ*፣ የሐመር መጽሔት ልዩ መጽሐፍ (ዐዲስ አበባ፣ ኀሐሴ 2002) ገጽ 91 - አጽንዖት የግል።

<u>ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቀን ይኖራል</u> እንጂ ዛሬ ኀጢአት ስንሠራ ከኀጢአታችን ለመንጻት የክርስቶስም ዳግመኛ መሰቀል የምንጠባባቅ አይደለንም። ይህንን ሁኔታ ግልጽ ሲያደርግ <u>ቅዱስ ጳውሎስ ለዘላለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል ብሎ ሕያው ዘለዓለማዊው አምላክ የፈጸመው የማስታረቅ ተልእኮ ዘለዓለማዊ መሆኑን አስረገጠን</u> እንጂ ክርስቶስ ዛሬም ያማልዳል[83] አላለም››።[84]

<u>ነገረ ክርስቶስ - ክፍል አንድ</u>

➪ **‹‹መሥዋዕት የሚቀርብላቸው ዕርቅ የሚደረግላቸው ወደ ተስፋው ይገቡ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ መሥዋዕት ማለት በግዕ፤ ቍርባን ማለት ኅብስት ወይን ሆኖ፤ እንዲሁም መሥዋዕት አቀራቢ <u>አስታራቂ ካህን ሆኖ</u> በቀራንዮ ላይ ሲገለጥ፤ ሥግው ቃል ክርስቶስ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ፣ ይቅር ባይ፣ ዋጋ ከፋይ ሆነ። ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕዝቡን ታረቀ፤ <u>አስታራቂ ሊቀ</u>**

---

[83] ጸሓፊው ክርስቶስ ‹‹ሲያስታርቀን ይኖራል››፣ በማለት ‹‹የፈጸመው የማስታረቅ ተልእኮ ዘለዓለማዊ መሆኑን...›› አስረግጠው ሲያስረዱ እንዳልነበረ ሐዋርያው ‹‹ዛሬም ያማልዳል አላለም›› የሚለውን ሐሳብ ያስፈሩት ከምን ተነሥተው እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም፤ ምንም ያቀረቡት አስረጂ የለምና። እርሳቸው በመካድ ሐዋርያው እንዲህ አላለም ብለው ቢያሰፍሩም በዚህ መጽሐፍ ምልጃ በዐዲስ ኪዳን በሚለው ርእስ ሥር ግን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ደጋግሞ የክርስቶስን አማላጅነት እንዴት እንዳሰፈረ መቅረቡ ይታወሳል።

[84] ብርሃኑ ኅበና፣ *ኖኅተ ሃይማኖት* (ዐዲስ አበባ፣ መስከረም 1986) ገጽ 130-131 - አጽንዖት የግል።

ካህናት፣ መታረቂያ መሥዋዕት ዋጋ ከፋይ ይቅር ባይ ሆነ››::[85]

ሁለቱ ኪዳናት

➪ ‹‹ ‹ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል› የተባለው አንድ ጊዜ በቀራንዮ ተሠውቶ ሳለ በመለኮት ሕያው ሆኖ በየጊዜው በወልደ እግዚአብሔር አምነው የሚመጡትን ሁሉ ሕይወት እየሰጠ ሊያስታርቅ የሚኖር በመሆኑ ነው››::[86]

የዕብራውያን ትርጓሜ በያዕቆብ ታድሮስ ማላቲ

➪ ‹‹ክርስቶስ መሥዋዕት፣ መሥዋዕትን አቅራቢ ሆኖ በሰማይ በአባቱ ቀኝ በዘለዓለማዊ ዙፋኑ አለ፡፡ የታረደ በግ ሆኖ እርሱ በመለኮቱ ለዘላለም ከአብ አይለይም፡፡ ነገር ግን ስለ እኛ ሲል የፍቅር መሥዋዕት ሆኖ ቀርቧል፡፡ ስለዚህ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ሊያደርገን ይቻለዋል፡፡ በደሙም ከራሱ ከአባቱና ከባሕርይ ሕይወቱ ጋር ያስታርቀናል፡፡ በአባቱም እቅፍ ውስጥ እንድንሆን ያደርጋል››::[87]

➪ ‹‹የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ መቀመጥ የመሥዋዕቱን ፍጹምነትና ኃይል ማሳያ ነው፡፡ መሥዋዕት እንደ በጎችና ፍየሎች ደም ሳይሆን ሕያው የሆነ መሥዋዕቱ ነውና፡፡ የሰውን ልጅ ለዘላለም

---

[85] ሮዳስ ታደሰ (መጋቤ ዐዲስ)፣ *ነገረ ክርስቶስ - ክፍል አንድ* (የካቲት 2008) ገጽ 341 - አጽንዖት የግል፡፡

[86] ኃየሎም በርሄ (መሪጌታ)፣ *ሁለቱ ኪዳናት* (ዐዲስ አበባ፣ 2002) ገጽ 339 - አጽንዖት የግል፡፡

[87] ታደለ ፈንታው (ዲያቆን) (ትርጕም)፣ *የዕብራውያን ትርጓሜ ታድሮስ ያዕቆብ ማላቲ* እንዳስተማሩት (2004) ገጽ 130 - አጽንዖት የግል፡፡

ሲያስታርቅ ይኖራል። ስለዚህ የሚያምን ክርስቲያን በአብ እቅፍ ሥር መሆን ይቻለዋል፤ በሰይጣን ላይ ድልን ይቀዳጃል››።[88]

ሐውልተ ስምዕ

➪ ‹‹ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ባደረገው ተልዕኮ ወይም የማስታረቅ አገልግሎት እስከ ምጽአት ድረስ ሰዎችን ሲያድንበት እንደሚኖር ለመግለጽ ነው እንጂ ዘወትር ይለምናል ለማለት አይደለም። ይኸውም በዕለተ ዓርብ የፈጸመው ተልዕኮ ወይም የማስታረቅ አገልግሎት በመስቀል ላይ ተፈጽሟል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹የእግዚአብሔር ጠላቶች ስንሆን በልጁ ሞት ታርቀናል› (ሮሜ 5÷8) ሲል በጻፈው መልእክት ይረጋገጣል። ጌታችን ወድዶና ፈቅዶ ባቀረበው በሥጋው መሥዋዕትነት በደሙ ፈሳሽነት ራሱን አንድ ጊዜ ለዘላለም በመሠዋት ያቀረበው ጸሎት የፈጸመው ዕርቅ ሰዎች ዘወትር ሲያስታርቃቸው ስለሚኖር ሐዋርያው ስለ እነርሱ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል። ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሊያድናቸው ይችላል ብሏል (ዕብራውያን 7÷25)››።[89]

ቀደም ሲል በቀረቡት መጻሕፍት ውስጥ በተለያየ መልኩ ክርስቶስ እውነተኛ አማላጅ መሆኑ ይታያል። እነዚህ መጻሕፍት በአንድም በሌላም መልኩ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መሆናቸው ኢየሱስ አማላጅ ነው የሚለው ትምህርት የሌሎች አብያተ እምነት ትምህርት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

---

[88] የቀደመው መጽሐፍ ገጽ 136 - አጽንዖት የግል።

[89] ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ *ሐውልተ ስምዕ* (ዐዲስ አበባ፣ 2004) ገጽ 202።

አንዳንዶች እዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት ሥራዎቻቸውም ሆነ በሌሎች መጻሕፍቶቻቸው የኢየሱስን አማላጅነት ፊት ለፊት ቢቃወሙም የመጽሐፍ ቅዱሱ እውነት ወጥሮ ሲይዛቸውና ማምለጫ ሲያጡ ግን ከዚህ በላይ በቀረበው መልኩ እርሱ ብቻ ዘለዓለማዊ አስታራቂ (አማላጅ) መሆኑን ለድርድር የማይቀርብ እንደ ሆነ ሲመሰክሩ ይታያሉ። የክርስቶስ አስታራቂነት ዘላለማዊ ከሆነ ሌላ አስታራቂ (አማላጅ) ያስፈለገው ለምን ይሆን? ክርስቶስ ያልሠራው ሥራ ኖሮ የእሱን ጉድለት ሊሞሉለት ይሆን? በክርስቶስ የማዳን (የማስታረቅ) ሥራ ውስጥ ምንም ጉድለት የለም! እርሱ ሙሉ የሆነ የማዳን ሥራ ነው የሠራው! በመሆኑም ከእርሱ ሌላ አስታራቂ አያስፈልገንም!!!

ክርስቶስ ፈራጅ ሆኖ ሳለ እንዴት ነው የሚያማልደው?

‹‹ኢየሱስ እንዴት ለፍርድ የሚመጣ ከሆነ እሱ ከሆነ ዳኛው ፈራጁ እንዴት አማላጅ ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ለመስጠት አይቻልም›› የሚሉት ‹‹መምህር›› ዘበነ፤ ክርስቶስ አያማልድም ለማለት የሚያቀርቡት ምክንያት አምላክነቱን ሲሆን ክርስቶስ ተመልሶ ስለሚመጣበት ሁኔታ ሲናገሩ ግን ‹‹<u>ለፍርድ ሲመጣ</u> ራሱ በተዋሐደው <u>በለበሰው ሥጋ ነው</u> ለፍርድ የሚመጣው። በተዋሐደው ሥጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ሲወለድ ሰው ሆነ በ30 ዘመኑ የተጠመቀው ሰው ስለሆነ ነው፤ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ የሚባለው እኮ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግሩ ሰው ስለሆነ ነው፤ መስቀሉን ተሸክሞ

ቀራንዮ ወጣ ስንል ሰው ስለሆነ ነው፣ እጆቹንና እግሮቹን ተቸነከሩ ስንል ሰው ስለሆነ ነው፡፡... እንጂ አምላክማ የሚዳበስ የሚጨበጥ ግዘፍ አካል የለውም ሰው ስለሆነ ነው እንጂ... የእኛ አምላክ አሁንም የትንሣኤያችን በኩር ነው... ይህ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው ኢየሱስ ተነሣ ስንል <u>አሁንም በሥጋው በተዋሐደው ሥጋ ተነሣ</u> ለደቀ መዛሙርቱ ታየ ለ500 ባልንጀሮች ተገለጠ ታየ... ይህ በሦስተኛው ቀን የተነሣው ክርስቶስ ኃያሉ አምላክ በዐርባኛው ቀን አረገ ሲያርግም ደቀ መዛሙርቱ አዩት÷ <u>ሲያዩት የቻሉት በተዋሐደው ሥጋ ስላረገ ነው</u>፡፡... ኢየሱስ በተዋሐደው ሥጋ አረገ <u>በተዋሐደው ሥጋ ይመጣል</u>›› ይላሉ፡፡

‹‹መምህሩ›› እንዳሉት ክርስቶስ ሲያገለግል የነበረው፣ በመስቀል ላይ የሞተውም ሆነ ከሞት ተነሥቶ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ያረገውም ሆነ ለፍርድ ተመልሶ የሚመጣው በተዋሐደው ሥጋ ከሆነ አሁን በአብ ቀኝ ለፍርድ ሲመጣ ይዞት የሚመጣውን ሥጋ ለብሶ ስላለ ስለ እኛ ይታያል መባሉ አንዳንድ ወገኖችን ለምን ቅር እንዳሰኛቸው ግልጽ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተባለው ክርስቶስ አሁንም ያማልዳል የሚባለው በለበሰው ሥጋ ነውና፡፡

‹‹መምህር›› ዘበነ የክርስቶስ መካከለኝነት ግራ የገባቸው ይመስላል፤ ‹‹መምህሩ›› ምን ያህል ግር እንዳላቸው የምንረዳው፡- ‹‹ኢየሱስን አማላጅ ብለህ ካልህ ለፍርድ ሲመጣ የሚፈርደው እሱ ነው አማልደኝ ልትለው ነው በዚያ ሰዓት?›› የሚለውን ንግግራቸውን ስንሰማ ነው፡፡

ምናልባትም ‹‹መምህሩ›› በክርስቶስ የፍርድ ስርዓት ወቅት ቅዱሳን ናቸው የሚያማልዱት ዓይነት ሐሳብ ሳይኖራቸው አይቀርም፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ ለፍርድ በሚመጣበት ወቅት ‹‹እባክህ ይቅር በለኝ›› የሚል ልመናም ሆነ ‹‹እኔ ላማልድህ እችላለሁ›› የሚል ታሪክ አይሠራም፡፡ ያ ሰዓት የፍርድ ሰዓት እንጂ የማስታረቅ (የማማለድ) አይደለም፡፡ እንኳ በፍርድ ወንበር ፊት ቆመን ይቅርና የፍርድ ሰዓት ሳይደርስ ራሱ ንስሐ ሳይገባ የሞተ ሰው ቢኖር ለንስሐ የነበረውን ጊዜ አጥቶታልና ከሞት በኋላ ሊያማልደው የሚችል ምንም አካል የለም፡፡ የክርስቶስ የመካከለኝነት ሥራ የሚጠቅመንም ሆነ ከፍርድ ልናመልጥ የምንችለው እዚህ ምድር ላይ ሳለን በስሙ ንስሐ በመግባት የጎጠአት ስርየትን ለመቀበል ፈቃደኞች ከሆንን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹... ሊፈርድ የሚመጣው ማን እንደ ሆነ ብቻ ሳይሆን ሰዎች ከፍርድ የሚያመልጡበትን እውነተኛ መንገድ ማሳየቱ ትክክለኛ አመለካከት ካለውና የመዳንን መንገድ ከሚያውቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ የሚጠበቅ››[90] ቢሆንም፤ ‹‹መምህር›› ዘበነ ግን እንዲህ ዓይነት ነገር አይታይባቸውም፡፡

የ‹‹መምህር›› ዘበነና የአድማጮቻቸው የስልክ ውይይት

‹‹መምህር›› ዘበነ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ለአድማጮቻቸው የስልክ መስመሩን ክፍት እንደ ሆነ በማሳወቅ ጥያቄ መጠየቅ የሚፈልጉ ሰዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ እድሉን ይሰጧቸውና የተለያዩ አድማጮች

[90] "ዘ ኢንድ ታይም" መጽሔት ቅጽ 1 ቍጥር 1 ገጽ 9፡፡

የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀርቡላቸዋል። ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች ለአንዳንዶቹ መልስ የሰጡበትን መንገድ ስንመለከት ራሳቸው ተሳስተው አድማጮቻቸውን ምን ያህል እያሳሳቱ እንደ ሆነ በቀላሉ መገንዘብ እንችላልን፤ በአድማጮች የቀረቡት ጥያቄዎችና መልሶቹን የተወሰኑትን እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፦

ዘሌዋውያን 12 ለጥምቀት?

ከዲሲ የደወሉትና የመጀመሪያው ጠያቂ የሆኑት አቶ ኤፍሬም ‹‹ወንድ ልጅ ሲወለድ በ40 ቀኑ ሴት ስትወለድ በ80 ቀኗ እንዲሁም ብዙ አባቶች አንድ ሰው ሲታመም ለ40 ቀን ወንድ ቢጠመቅ ሴት ልጅ ለ80 ቀን ብትጠመቅ የሚባል ነገር አለ›› በማለት ስለዚሁ ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል። ‹‹መምህር›› ዘበነም እንደሚከተለው መልስ ሰጥዋል፤

> ወንድ በ40 ቀን የሚጠመቀው ሴት በ80 ቀን የሚጠመቁበት ምክንያት አላቸው፤ በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 12 እንደተጻፈው አንዲት ሴት÷ ሴት በምትወልድበት ሰዓት የመንጻትዋ ጊዜ የሚፈጸመው በዚያ ላይ ተጽፏል። ቀኑን ብታየው ስሌቱን ብትደማምረው ታገኘዋለህ ዘሌዋውያን 12 ላይ ያለውን እንደዚሁም ደግሞ በኩፋሌ 4÷9 ላይ ደግሞ እንደምንመለከተው ሥላሴ አዳምን በፈጠሩ በ40ኛው ቀን ላይ ሔዋንን በፈጠሩ በ80ኛው ቀን ላይ ወደ ገነት ገብተዋል፤ ስለዚህ ከዚህ በተነሣ መልኩ እኛ

ጥምቀታችንን በ40ኛው በ80 ቀን ሊሆን በቅቷል። ብዙው ጊዜ በብሉይ ኪዳን ያሉ በአዲስ ኪዳን ብዙ ፍጻሜ ስላላቸውና የተፈጸሙ ስለሆነ በዚያ ዓይነት መልኩ ነው ሁሉ ነገር የሚደረገውና በዚያ ነው። ለዚህም ደግሞ ህጻን በመሆናቸው አንዳንድ ሰዎች ድንገት እንዴት ሊጠመቁ ይችላሉ? የሚል አባባል ይኖራል። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር አምላክ ልጅነት ለማግኘት ስለሆነ በልጅነታቸው ወደ እግዚአብሔር ይመጣሉ እንደ ክርስቲያን ልጆች ጥምቀቱ ይሰጣቸዋል።

ጥምቀትን በተመለከተ ሰዎች አምነው መጠመቅ አለባቸው የሚል አንድ ቡድንና የለም ቤተ ሰብ የሚያምን ከሆነም በልጅነታቸው መጠመቅ ይችላሉ የሚል ሌላ ቡድን መኖሩ ይታወቃል። የልጅነትን ጥምቀት ከሚቀበሉት ውስጥ አንዷ ቤተ ክርስቲያናችን ስትሆን ለዚህም እንደ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርበው ቀደም ሲል ‹‹መምህር›› ዘበነ የጠቀሱት ምዕራፍ ነው።

በምንባቡ በዝርዝር የሰፈረው አንዲት አይሁዳዊት ሴት ከወለደች በኋላ የመንጻትዋን ወራት እስክትፈጽም ድረስ ማድረግ የሚኖርባትን ስርዓት እና ስርዓቱን ለመፈጸም ምን ያህል ቀን መታገስ እንዳለበት ወይም ለምን ያህል ቀናት የረከሰች እንደምትሆን ነው።

ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ÷ <u>ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት</u>፤ እንደ

ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች። <u>በስምንተኛው ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ</u>። ከደምዋም <u>እስከምትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ</u>፤ የመንጻትዋ ቀን እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰን ነገር አትንካ÷ ወደ መቅደስም አትግባ። ሴትም ልጅ ብትወልድ እንደ <u>መርገምዋ ወራት ሁለት ሳምንት ያህል የረከሰች ናት</u>፤ ከደምዋም <u>እስከትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ</u> (ቍጥር 2-5 - አጽንዖት የግል)።

ከላይ የቀረበው የዘሌዋውያን ምንባብ ከጥምቀት ጋር የተገናኘ ነገር የሌለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን ልጆቹን ሳይሆን እናቲቱን መሠረት አድርጎ የተሰጠ ትእዛዝ ነው። ከልጆቹ ውስጥ ወንዱን ልጅ ‹‹ይገረዝ›› ከማለት ያለፈ ሴቷን ልጅ በተመለከተ ምንም ትእዛዝ ሳይስቀምጥ ነው ያለፈው። ቤተ ክርስቲያን ይህን ጥቅስ መሠረት አድርጋ ሥርዓት መሥራት የሚገባት ቢሆን እንኳ ከእናትየው ጋር በተገናኘ እንጂ ወደ ልጆቹ እንድታስብም ሆነ እንድትመለከት የሚያደረጋት ምንም መሠረት የለም።

ሌላው የ‹‹መምህሩ›› ንግግር ‹‹ብዙው ጊዜ በብሉይ ኪዳን ያሉ በአዲስ ኪዳን ብዙ ፍጻሜ ስለአላቸውና የተፈጸሙ ስለሆነ በዚያ ዓይነት መልኩ ነው ሁሉ ነገር የሚደረገውና በዚያ ነው›› የሚል ነው። ‹‹መምህሩ›› ይህን ንግግሩን የተናገሩበት ምክንያት የዘሌዋውያንን ምንባብ የማያውቁት ሰዎች ክፍሉ የትንቢት ክፍል እንደ ሆነ በማሰብ የእርሳቸውን ንግግር ያለምንም ተቃውሞ እንዲቀበሏቸው በማሰብ

ይመስላል፡፡ ነገር ግን ይህ ክፍል ከክርስቶስ መምጣት በኋላ የቀሩና ከእርሱ መምጣት በፊት እንደ ሕግ ሆነው እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ በሞግዚትነት ለማገልገል ከተቀመጡት የሙሴ ሕግጋት አንዱ መሆኑ ይታወቃል (ገላትያ 3÷24)፡፡ ከእነዚህ በርካታ ሕግጋት ውስጥ እግዚአብሔር ለዚያ ዘመን ሰው ሲጠቀምበት የነበረና አሁን ግን የማይደረጉ ነገሮችን በማሳየት የ‹‹መምህሩ›› ንግግር የግል አስተምህሮን ከመደገፍ አንጻር እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን ማቅረብ አስፈላጊ ሆኗል፤

- የብሉይ ኪዳን ሕግጋት በዐዲስ ኪዳን ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ከሆነና አሁንም እኛ እነዚያን ሕግጋት እንድንጠብቅ (እንድንፈጽም) የሚጠበቅብን ከሆነ የሙሴ ሕግ ለምጻም የሆኑት ሰዎች ከሰፈር ውጪ እንዲሆኑ ስለሚያዝ እኛም ይህን ሕግና ስርዓት ልናከብር የግድ ይሆንብናል ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በክርስቶስ የሆነልን ዐዲሱ ኪዳን ዋጋ የሌለው ከንቱ ነገር መሆኑ ነው ማለት ነው (ዘሌዋውያን 13÷45-46)፡፡
- በሙሴ ሕግ መሠረት ሊቀ ካህኑ ወደ ቤተ መቅደስ ውስጠኛው ክፍል የሚገባው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር፤ በዘሌዋውያን ላይ ያለው የመንጻት ስርዓት አሁንም በእኛ ዘመን የሚሠራ ከሆነ የቤተ መቅደሱም ስርዓት የማይጠበቅበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለምና አሁን እኛ ይህን ሕግ ልንፈጽመው ግድ ነው ማለት ነው (ዕብራውያን 9÷7)፡፡
- ‹‹እግዚአብሔርም ከመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ ሲል ተናገረው፦ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ

ብለህ ንገራችው...›› አለ የሚለው ኦሪት ዘሌዋውያን ‹‹... ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች...›› ስለሚቀርበው መሥዋዕት ይናገራል። ለሙሴ የተነገረው ትእዛዝ ሲያበቃም ይህ ‹‹... የሚቃጠል መሥዋዕት የእሳት ቍርባን በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ...›› እንደሆነ ይገልጻል (ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1)። ይህ ለነቢየ እግዚአብሔር የተሰጠው ትእዛዝ አሁን በቤተ ክርስቲያናችን የሌለ መሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሱን መጽሐፍ መታዘዝ ትታለች አያስብላትም። ምክንያቱም አሁን ከዚህ ሕግ ነጻ ነንና።

መጽሐፈ ኩፋሌ

ሌላው ‹‹መምህር›› ዘበነ ለማስረጃነት ያቀረቡት መጽሐፈ ኩፋሌን ነው። መጽሐፈ ኩፋሌ ከእግዚአብሔር ቃልና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ጋር የማይስማማ መልእክት የያዘ መጽሐፍ በመሆኑ ለሃይማኖታዊ ጉደይ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የማይገባው መጽሐፍ ነው።[91]

መጽሐፈ ኩፋሌ	መጽሐፍ ቅዱስ እና የቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት
እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው የዕንቍ ጽላት ነው (1÷1)።	የዕንቍ ጽላት ሳይሆን የድንጋይ ጽላት ነው (ዘዳግም 4÷13)።

[91] መጽሐፈ ኩፋሌ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር የማይስማማ መሆኑን በዚህ መጽሐፍ መጠነኛ ማሳያ ተሞክሯል። ነገር ግን መጽሐፉ ምን ዓይነት ችግር አለበት የሚለውን በተሻለ ሁኔታ ለማየት ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› የሚለውን መጽሐፍ መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

እግዚአብሔር ሔዋንን ሲፈጥር እንዲሁም የባቢሎንን ግንብ ለመሥራት ጥረት ሲያደርጉ የነበሩትን ሰዎች ቋንቋቸውን ሲደባልቅባቸው መላእክትን አማክሮ ነበር (4÷4-5)።[92]	‹‹የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ÷ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? የፍርድንም መንገድ ማን አስተማረው? እውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?›› (ኢሳይያስ 40÷13-14)
‹‹ሴት›› በመባል ለተጠራው የቃየል ምትክ ስሙን ያወጣለት አዳም (አባቱ) ነው (5÷13)።	‹‹ሴት›› የሚል ስም ያወጣችው እናቱ ነች እንጂ አባቱ አይደለም (ዘፍጥረት 4÷25)።

[92] እንዲህ ዓይነት ትምህርትና እምነት ያለው በቤተ ክርስቲያናችን አይደለም። ከዚህ ይልቅ ግን በልማድ ‹‹ኢየሱስ ብቻ›› ተብለው ከሚታወቁትና ለራሳቸው ‹‹የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን›› ብለው ስም ከሰጡት ሰዎች መካከል የሆኑት ኤልያስ ሽባባው ዘፍጥረት ዐሥራ አንድን መነሻ በማድረግ ‹‹... እግዚአብሔር ሲወርድ ክብሩን የሚሸከሙ መላእክት አብረውት ይወርዳሉ።... ኪሩቤል ማለት በዛ ያለ የመላእክት ስብስብ ከሆኑና የእግዚአብሔርን ክብር የሚሸከሙ ከሆነ እኛ ማለቱ ለሥራ የሚጠቀምባቸውን መላእክት ወይም ሠራተኞቹን እንደ ዕቃ ሳይቈጥር አብረውት መሥራታቸውን ለመግለጽ መናገሩን ያመለክታል እንጂ ለሌሎች እግዚአብሔሮች አብረውት ነበሩ ወይም ሠሩ አልያም እግዚአብሔር ሥላሴ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊወስደን አይገባም...›› ያሉትን መመልከት ትምህርቱ የሰባልዩሳውያን መሆኑን ለመረዳት አያስችግርም (ኤልያስ ሽባባው (ፓስተር)፣ የሥላሴ አጠያያቂ ምሥጢር በአንድ አምላክ ብርሃን ሲመረመር (የካቲት 2008 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 194)። ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ምን ነክቷት ይሆን እንዲህ ያለውን ትምህርት የያዘውን መጽሐፍ የእኔ መጽሐፍ ነው ብላ የያዘችው?

በተፈጥሯቸው ሥጋዊ ነገር ጋር ያልተነካኩት መላእክት ትዳር ውስጥ ገብተው፤ የልጆች አባት ሆነው ነበረ (6÷9)።	‹‹ቅዱሳን መላእክት ጾታ የላቸውም ነገር ግን በወንድ ጾታ ይጠራሉ አይጋቡም አያገቡም››፣ ‹‹መላእክት አንድ ጊዜ የተፈጠሩና በየጊዜው የማይባዙ ናቸው››[93]።

መጽሐፈ ኩፋሌ ቀደም ሲል በቀረቡት ሐሳቦቹ እና በሌሎች ትምህርቶቹ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርትም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደማይስማማ ማየት ይቻላል። ከዚህም በመነሣት እንዲህ ያለውን መጽሐፍ ለሃይማኖታዊ ጉደይ እንደ ማስረጃ አድርጎ መቀበል ግልጽ የሆነውን ስሕተቱን እንደማጽደቅና ከስሕተቱም ጋር እንደ መተባበር የሚቈጠር ይሆናል።

መዝሙረ ዳዊት 108÷14 ለጾም?

ሌላው ከቨርጂኒያ የደወሉትና እኅተ ማርያም የተሰኙት ሴት የጠየቁት ጥያቄ ‹‹በጾም ጊዜ ለምንድን ነው ቅባትና ሥጋ የማንበላው?›› የሚል ሲሆን ‹‹መምህር›› ዘበነም

[93] የማነ ብርሃን ገበየሁ (ሊቀ ጎሩያን)፣ የጽድቅ በር እነሆ (1997) ገጽ 5። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት (ዐዲስ አበባ፣ ሐምሌ 1988) ገጽ 54። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ የጥር ድርሳነ ሚካኤል (ዐዲስ አበባ፣ 1999) ገጽ 121። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መጻሕፍት ብሉያት ፪ቱ (ዐዲስ አበባ፣ 1999)፣ ገጽ 309። ብርሃኑ ኅበና፣ ኖኅተ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ መስከረም 1986) ገጽ 60። ብርሃነ ሥላሴ አስፋው (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመከራ ጉዞ (በታሪክ ውስጥ) (2006) ገጽ 65። ያረጋል አበጋዝ (ዲያቆን) መድሎተ ጽድቅ (ዐዲስ አበባ፣ መጋቢት 2007) ገጽ 407፡ 447። የያህ ነጋሽ (ዶክተር/ዲያቆን) ኔፍሊም (ዐዲስ አበባ፣ ሐምሌ 2006) ገጽ 175።

‹‹በመጀመሪያ የኃይል ሰጪ ወይም እንደ ቅቤ ሥጋ እነዚህ የመሳሰሉ የማንበላበት ምክንያት ቅዱሳን በሚጸሙበት ሰዓት እነዚህን ምግቦች ተከልክለው ስለ ነበረ እኛም በዚያ ሕግ መሠረት ነው የምንጸመው›› የእኛ እምነታችን ሁሉ ነገሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ነው ለምሳሌ ዳዊት እንደሚጸመው ዳንኤል እንደሚጸመው ነው እኛ የምንጸመው፡፡ ለምሳሌ ዳዊት ሲጸም ምን አለ? መዝሙረ ዳዊት 108÷24 ላይ ሰውነቴ ቅቤ በማጣት ከሳ፤ በጾም ሰውነቴን አደከምኩት ይላል፡፡ ስለዚህ ቅቤን አይበላም ነበር ሲጸም ዳዊት…›› በማለት ነበር መልስ የሰጡት፡፡

የ‹‹መምህሩ›› ለየት ያለ ባሕርይ መጽሐፍ ቅዱስ የማይለውን ነገር ‹‹መጽሐፉ እንዲህ ይላል›› ለማለት ያላቸው ድፍረት ነው፡፡ አሁን ከቀረበው ንግግራቸው ብቻ ከእግዚአብሔር ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሊያቀርቡለት የማይችሉት አንዱ መልእክታቸው ‹‹ቅዱሳን በሚጸሙበት ሰዓት እነዚህን ምግቦች ተከልክለው ስለ ነበር እኛም በዚያ ሕግ መሠረት ነው የምንጸመው›› የሚለው ነው፡፡ ተከለከሉ የተባሉትን ቅዱሳንን ለማሳየትም ‹‹ለምሳሌ›› በማለት ‹‹ዳዊት ሲጸም ምን አለ? መዝሙረ ዳዊት 108÷24 ላይ ሰውነቴ ቅቤ በማጣት ከሳ፤ በጾም ሰውነቴን አደከምኩት ይላል›› የሚለውን ያቀርባሉ፡፡ ከምንባቡ ውስጥ ግን ትእዛዙን (ክለከላውን) ሊያሳዩ አልቻሉም፡፡

እርሳቸው የጠቀሱትን ጥቅስ በማስቀመጥ ትእዛዝ የተባለውና እኛም በዚያ ሕግ መሠረት ነው የምንጸመው ለማለት ምክንያት የሆነው ምን እንደ ሆነ መፈልጉ ተገቢ

ነው፤ እርሳቸው አንድ ቍጥር ብቻ (ቍጥር 24) የጠቀሱ ቢሆንም ሕግ የተባለውን ለማግኘት ከፍና ዝቅ ብሎ መመልከቱም ተገቢ በመሆኑ ከቍጥር 23-25 ለማቅረብ ተሞክሯል፤ ‹‹እንዳለፈ ጥላ አለቅሁ፥ እንደ አንበጣም እረገፍሁ። ጕልበቶቼ በጾም ደከሙ፤ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ። እኔም በእነርሱ ዘንድ ለነውር ሆንሁ፤ ባዩኝ ጊዜ ራሳቸውን ነቀነቁ››። ‹‹መምህሩ›› ከዚህ ምንባብ ላይ ትእዛዝ የመሰላቸው የትኛው እንደ ሆነ ሊያሳዩ ሞክረው ቢሆን ሐሳባቸውን ለመረዳት የተሻለ ይሆን ነበር።

‹‹መምህሩ›› ‹‹የእኛ እምነታችን ሁሉ ነገሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ነው›› የሚልም ሐሳብ አንሥተዋል። ይህን ያሉት በጾም ወቅት የእንስሳ ተዋጽዖ መብላት የለብንም ለሚለው ስብከታቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። የእንስሳ ተዋጽዖ መመገብም ሆነ አለመመገብ ኀጢአትም ጽድቅም አይደለም። እንዲህ ያለ ትእዛዝ በቅዱስ መጽሐፍ የሚገኝ ባለመሆኑ ይህን እንደ ሕግ ለማስቀመጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለም።

‹‹መምህሩ›› እንዳሉት እምነታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው የምንል ከሆነና ለዚህም ዳዊትንና ዳንኤልን ከጠቀስን ዳዊትና ዳንኤል እንዳደረጉት ማቅ ለብሰንና በራሳችን ላይ አመድ ነስንሰን ለምን አንጾምም? ዳዊትና ዳንኤል ራሳቸውን ከቅቤና ከሥጋ መከልከል ብቻ ሳይሆን እንዲህ እንዳደረጉ ቃሉ ይናገራልና (መዝሙረ ዳዊት 34÷13። ዳንኤል 9÷3)።

የፕሮቴስታንት አማኝ ‹‹ኢየሱስ አይፈርድም›› አሉ!?

የስብከት ሲዲውን ገዝቼ የሲዲው ሽፋን ላይ ‹‹መላውን አድማጭ ያነጋገረ›› የሚለውን የጽሑፍ መልእክት ስመለከት ስብከቱን ለመስማት በጣም እየጓጓሁ ነበር ወደ ቤቴ የሄድኩት፡፡ ቤቴ ገብቼም ስብከቱ ከመጀመሩ በፊት ‹‹ሊፈርድ የሚመጣው ማን ነው? በሚል ርእስ ባስተማሩት የሬዲዮ ትምህርት ላይ በተለይም ኢየሱስ ክርስቶስ አይፈርድም በማለት የፕሮቴስታንት አማኝ የተናገሩት ልዩ የስልክ መልእክትም አለ›› የሚለውን የድምጽ መልእክት ሳዳምጥ ለመስማት የበለጠ ፍላጎቴ ጨመረ፡፡ ነገር ግን የተባለው ቦታ ጋር ደርሼ ወ/ሮ ዘነበች የሚባሉት ሴት የተናገሩትና በስብከቱ መግቢያ ላይ የተባለው አልጣጣምልህ ቢለኝ ደግሜ ለመስማት ተገደድኩ፡፡

በእርግጥ የወ/ሮ ዘነበች ንግግር አግባብነት የሌለውና ለማንም ምንም የማይጠቅም ቢሆንም÷ ለስብከቱ መግቢያ አድርገው ባቀረቡት መልክ ግን የተናገሩት ነገር እንደሌለ አንባቢው እንዲረዳው ከ‹‹መምህሩ›› ጋር የነበራቸውን ውይይት ቃል በቃል እንዲሰፍር አድርጌአለሁ፤

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹ይሄ መልእክት ቀጥታ ለዘበነ ነው፡፡ ዘበነ ትምህርትህን እሰማለሁ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ÷ በዘመኑ የተነሣህ የክርስቶስ ጠላት አንቲ ክራይስት ነህ፡፡ ሳያል ሆይ ሳያል ሆይ ለምን ታሳድደኛለህ? አለ÷ አንተ የክርስቶስን ተከታዮች የኢየሱስን ተከታዮች የምታሳድድ በዘመኑ የተነሣህ የክርስቶስ ጠላት…››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹እግዚአብሔር ይስጥልን››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹የክርስቶስ ጠላት፤ ፍርዱ አሁን በቅርብ ጊዜ ኢየሱስ ይመጣል፤ በእርግጥ ግን ለእንዳንተ ዓይነቱ ፍርድ ነው የሚመጣው፡፡ በዘመኑ የተነሣህ ክርስቶስን የምታሳድድ እናቶችን የምታሳሳት...››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹አንድ ጥያቄ ልጠይቆት››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹አሁን ነው ስለ ክርስቶስ ማስተማር የጀመርከው፤ ፕሮቴስታንቶች የዛሬ ስንት ዓመት ነው ክርስቶስ መምጣቱን የሰበኩት? አሁን ግን ከፕሮቴስታንቶች ኮርጀህ ነው ስለ ክርስቶስ መስበክ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ዛሬ፣ ነገር ግን ይህ ፍርድ ላንተ ነው፤ ወዮልህ ላስተማርከው ለዚህ ሕዝብ ተጠያቂ ነህ፤ አንድ ቀን በክርስቶስ ፊት መልስ ትሰጥበታለህ››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹ወ/ሮ ዘነበች አንድ ጥያቄ ልጠይቆት››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹ምንም ዓይነት ጥያቄ አልፈልግም፤ አውቅሀለሁ አንተን አሳሳች የክርስቶስ ጠላት››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹አይሳሳቱም ግድ የለም ልጠይቆት፤ ምን አስፈራዎት? ወንጌል አይደል እንዴ?››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹ምንም አልፈራም››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹ወይም ከፓስተሩ ጋር ለምን አያገናኙኝም?››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳሳትክ አሳሳች የክርስቶስ ጠላት ነህ ብዬአለሁ በዘመኑ የተነሣህ››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹አንድ ጥያቄ ልጠይቆት››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹ከመንገድህ ተመለስ››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹እንዲመልሱኝ አንድ ጥያቄ ልጠይቆት››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹አሁንም ክርስቶስን ስበክ››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹በዚህ እምነት ነው የሚድኑት እርስዎ? በእንዲህ በንግግር?››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹በእምነት አይደለም ፕሮቴስታንቶችን ተዋቸው፤ ሁል ጊዜ ስለ ፕሮቴስታንቶች ጥላቻ ነው ስትሰብክ የምሰማህ፡፡ ነገር ግን ዝም ብለህ ወንጌልን ስበክ እውቀቱ ስለሌለህ ሁልጊዜ ጥላቻ ነው የምትሰብከው››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹እውቀቱ እንደሌለኝ በምን አወቁ? ለምን ታዲያ…››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹አንድ ቀን አምላክ ፊት ትቀርባለህ፤ ትጠየቅበታለህ››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹በእንግሊዘኛ ከገባዎት በእንግሊዘኛ ልጠይቆት፤ አንድ ጥያቄ አለኝ›› (ቀደም ብሎ ወ/ሮ ዘነበች በእንግሊዘኛ ስለተናገሩ ነው ‹‹መምህሩ›› ይህን የተናገሩት)

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹አማርኛ መናገር እችላለሁ››

‹‹መምህር›› ዘበነ፡- ‹‹እሺ በአማርኛ አይ ደበላለቁብን’ኮ አንድ ጥያቄ ልጠይቆት? የፕሮቴስታንት እምነት መቼ ነው የተመሠረተው?››

ወ/ሮ ዘነበች፡- ‹‹ስለ ዓመተ ምሕረቱ ምን አገባህ አንተ?››

እዚህ ጋር የ‹‹መምህር›› ዘበነና የወ/ሮ ዘነበች ውይይት ያበቃና ‹‹መምህሩ›› የግላቸውን አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ውይይታቸውን ቃል በቃል ለማስቀመጥ ያስፈለገበት ምክንያት ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው

‹‹በተለይም ኢየሱስ ክርስቶስ አይፈርድም በማለት የፕሮቴስታንት አማኝ የተናገሩት ልዩ የስልክ መልእክትም አለ›› የተባለውና የፕሮቴስታንት አማኝ የሆኑት ሴት የተናገሩት አንድ ስላልሆነ ‹‹መምህሩ›› ምን ያህል ሕዝቡን እያሳሳቱት እንደ ሆነ ለማሳየት ተብሎ ነው። በ‹‹መምህሩ››ና በወ/ሮዋ መካከል ስለ ክርስቶስ ፈራጅነትም ሆነ አማላጅነት የተደረገ ምንም ዓይነት ውይይት በሌለበት ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ አይፈርድም ብለዋል›› መባሉ ለምን እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም።

የእግዚአብሔር ቃል አገልጋይ ነኝ ከሚል ሰው እንዲህ ያለ ሐሰተኛ ንግግር አይጠበቅም። እንዲህ ያለውን ነገር የፈጸሙት ደግሞ ሕዝቡን ከተሳሳተ ሃይማኖት አውጥቼ ወደ እውነተኛው ሃይማኖት እመራለሁ የሚሉ ‹‹ሃይማኖተኛ›› ሰው መሆናቸው በጣም አስገራሚ ነው። ማንም ሰው ሰምቶ ሊፈርድ በሚችለው እንዲህ ያለ ሐሰተኛ ንግግር ከቀረበ ለመረዳት በማንችላቸው ነገሮች አለመዋሸታችንን ምን ያህል እርግጠኛ ለመሆን እንችል ይሆን?

ዋቢ

መልከ ጼዴቅ (አባ)፣ (1984 ዓመተ ምሕረት)። ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ። ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

መሓሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ (ጥቅምት 23 1948 ዓመተ ምሕረት)። የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው። ዐዲስ አበባ።

ማኅበረ ቅዱሳን፣ (ዐዲስ አበባ፣ ነሐሴ 2002 ዓመተ ምሕረት)። ሐመረ ተዋሕዶ፤ የሐመር መጽሔት ልዮ መጽሐፍ። ዐዲስ አበባ፣ አማኑኤል ማተሚያ ቤት።

ማኅበረ በሶር፣ (ሐምሌ 2002 ዓመተ ምሕረት)፣ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቍጥር 39። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ሮዳስ ታደሰ (መጋቤ ዐዲስ)፣ (የካቲት 2008 ዓመተ ምሕረት)። ነገረ ክርስቶስ - ክፍል አንድ። ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግል. ማኅበር።

ብርሃኑ ኅበና፣ (መስከረም 1986 ዓመተ ምሕረት)፣ ኖኅተ ሃይማኖት። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ፣ (1987 ዓመተ ምሕረት)። ዐዲስ አበባ፣ ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ። ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ታደለ ፈንታው (ዲያቆን) (ትርጕም)፣ (2006 ዓመተ ምሕረት)። የቅዱስ ዮሐንስ መልእክታት፤ ታድሮስ ያዕቆብ ማላቲ እንዳስተማሩት። ዐዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።

ቴዎድሮስ ደመላሽ (ጥር 2010 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ እትም)። <u>ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን</u>። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

_____፣ (ሚያዝያ 2009 ዓመተ ምሕረት)። ኢየሱስ እውነተኛ አማላጅ ጻድቅ ፈራጅ። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (ሐምሌ 1988 ዓመተ ምሕረት)። <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት</u>። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1994 ዓመተ ምሕረት)። <u>ዐዲስ ኪዳን በግእዝና በዐማርኛ</u>። ዐዲስ አበባ፣

_____፣ (2004 ዓመተ ምሕረት)። <u>መጽሐፈ ዲድስቅልያ</u>። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (ግንቦት 1988 ዓመተ ምሕረት - ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ)። <u>የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው</u>። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1986 ዓመተ ምሕረት)። <u>ሃይማኖተ አበው</u>። ዐዲስ አበባ፣

_____፣ (2010 G.C)። <u>መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ</u>። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1983 ዓመተ ምሕረት)። <u>ውዳሴ ማርያም ቅዱስ ኤፍሬም የደረሰው ንባቡና ትርጓሜው</u>። ዐዲስ አበባ።

ኃየሎም በርሄ (መሪጌታ)፣ (2002 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)። ሁለቱ ኪዳናት። ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኃላ. የተ. የግል. ማኅበር።

ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ (2004 ዓመተ ምሕረት)። ሐውልተ ስምዕ። ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ (1919 ዓመተ ምሕረት)። ኅሊና ጽባሕ። (የታተመበት ቦታውና ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)።

አለማየሁ ሞገስ ደርሶ (ቀደሰ)፣ (1987 ዓመተ ምሕረት)። ሁሉም ሁሉን ይወቅ። ዐዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

አሐዱ አስረስ (ዲያቆን)፣ (መስከረም - ጥቅምት 1997 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)። ኢየሱስ ፈራጅ ወይስ አማላጅ? እሌኒ ማተሚያ ቤት።

አበራ በቀለ (ሊቀ ጉባኤ)፣ (2008 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)። ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት። ቲ ዜድ ኅትመትና ማስታወቂያ።

አድማሱ ጅንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ (የካቲት 1989 ዓመተ ምሕረት)። ኩሎሐ ሃይማኖት። ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ (1992 ዓመተ ምረት)። ምልጃ፣ እርቅና ሰላም። ዐዲስ አበባ፣ የታተመበት ቦታ ያልተገለጸ።

አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ (ሐምሌ 1979)። ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ። (ዐዲስ አበባ)።

አፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ) - መምህረ ግእዝ ወቅኔ፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)። ሀገረ-መጻሕፍት፤ ሰዋስው ግእዝ ወዐሚርኛ። አሳታሚ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ኤልያስ ሽባባው (ፓስተር)፣ (የካቲት 2008 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)፣ የሥላሴ አጠያያቂ ምሥጢር በአንድ አምላክ ብርሃን ሲመረመር። ሪላ ማተሚያ ቤት።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ (1948 ዓመተ ምሕረት)። መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ወልደ ሚካኤል ቶሎሳ፣ (2005 ዓመተ ምሕረት)። በእንተ ሰማንያ አሐዱ። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የማነ ብርሃን ገበየሁ (ሊቀ ጎሩያን)፣ (1997 ዓመተ ምሕረት)፣ የጽድቅ በር እነሆ። የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (2000 ዓመተ ምሕረት)። ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምእመናን የቅዱስ እስጢፋኖስ ጉባኤ፣ (ጥቅምት 1990 ዓመተ ምሕረት)፣ ፍኖተ ብርሃን። ንግድ ማተሚያ ቤት።

ዘበነ ለማ (መምህር)፣ ኦርቶዶክሳዊ መልስ የተሰኘ የቴፕ ካሴት።

_____፣ ሊፈርድ የሚመጣው ማን ነው?

ገብርኤል (አባ)፣ (1990 ዓመተ ምሕረት)። <u>ክብረ ቅዱሳን</u>። ዐዲስ አበባ፣ ግራፊክስ አታሚዎች።

ጌታቸው ተረፈ (መምህር)፣ (መስከረም 2010 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)። <u>መልሕቅ - ክፍል ሁለት</u>። አይቤክስ ማተሚያ ቤት።

_____፣ (የካቲት 2011 ዓመተ ምሕረት)። <u>ተፋልሶ - ክፍል አንድ</u>። በረከት ማተሚያ ቤት።

ጊዮርጊስ (አባ)፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>አርጋኖን፤ የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ</u>። ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

_____፣ (2007 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>አርጋኖን፤ የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ</u>። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን። ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማተሚያ ቤት።

ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (አባ)፣ ተርጓሚ ሕሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ (መጋቢት 2001 ዓመተ ምሕረት)። <u>መጽሐፈ ምሥጢር</u>። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

እነዚህን ጠቃሚ መጻሕፍት አንብበዋቸዋል?









ካላነበቧቸው ሊያነቧቸው ይገባል